ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 018 መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








# በአዲስ አበባ 20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

- በምርቃቱ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ማዕድ አጋርተዋል

ገጽ 6













ወይዘሮ እናትነሽ ታመነ

## ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ሰባት ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ እየሠራ ነው

ገጽ 6

## በሰሜን ጎንደር በተከሰተው ድርቅ 452 ሺህ ዜጎች ተጎድተዋል

- 202 ሺህ ዜጎች አስቸኳይ የምግብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር በተከሰተው ድርቅ 452 ሺህ ዜጎች መጎዳታቸውንና 202 ሺህ ዜጎች አስቸኳይ የምግብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን የሰሜን ጎንደር ዞን አደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ሰላምይሁን ሙላት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ ከግንቦት

በሰሜን ጎንደር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ ሰላምይሁን ሙላት

## ከክልሉ የማዕድን ወጪ ንግድ 20 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት በክልሉ የማዕድን ወጪ ንግድ 20 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱን የአማራ ክልል የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ፡፡ በዘርፉ ለ45 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየተሠራ እንደሚገኝም ተመላክቷል፡፡

በአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት ከማዕድን የወጪ ንግድ 20 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል፡፡

የተቀመጠውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የታቀደው፤ በዋናነት ከሁለት ማዕድናት ገቢ እንደሆነ የተናገሩት ምክትል ኃላፊው፤ የመጀመሪያው በወርቅ ምርት ሲሆን፤ በጎንደርና በተለያዩ አካባቢዎች የወርቅ ክምችት መኖሩ በጥናት በመረጋገጡ በቀጣይ ባለሀብቶችን ለማሰማራት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ከክልሉ የማዕድን ወጪ... ወደ ገጽ6 ዞሯል








# የመቐለን ከተማ የውሃ እጥረት ለመፍታት እየተሠራ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- በመቐለ ከተማ ያለውን የውሃ እጥረት ለመፍታት የረጅምና የአጭር ጊዜ መፍትሔዎች ተበጅተው እየተሠራ መሆኑን የመቐለ ከተማ የውሃ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ገለፀ።

የመቐለ ከተማ የውሃ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር አሸናፊ ዘአብርሃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በመቐለ ከተማ ለሚኖረው አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ ሰፊ የውሃ አቅርቦት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ለከተማዋ ሕዝብ የውሃ ፍላጎት በቀን 120 ሺህ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊው፤ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በመቅረብ ላይ ያለው 30 ሺህ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ ብቻ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ይሰጣሉ ተብለው የተያዙ ፕሮጀክቶች በሁለት የተከፈሉ መሆኑን አብራርተው፤ የረጅምና የአጭር ጊዜ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተቀምጠው እየተሠራ ነው ብለዋል።

የአጭር ጊዜ መፍትሔ ይሆናል ተብሎ የተቀመጠው በጣም ለተቸገሩ ሰዎች በቦቴ ውሃ ማዳረስ መሆኑን ተናግረዋል። በመቐሌ አካባቢ የሚገኘው «የገረብ ሰገን» ግድብ በሙሉ አቅም እንዲሠራ ከበጎ አድራጊዎች ጋር በመነጋገር የመለዋወጫ ዕቃ እንዲሟሉ በማድረግ በፍጥነት አገልግሎት ማስጀመርም ከተያዙ የአጭር ጊዜ የመፍትሔ ሥራዎች መካከል ሌላው ነው ብለዋል።

የውሃ ችግሩን ለማቃለል ትላልቅ ድርጅቶች የራሳቸው የውሃ ጉድጓድ እንዲያዘጋጁ እየተነጋገርን ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

ከፌዴራልና ከክልሎች ጋር በመግባባት ተጀምሮ የቆየው «የገረብ ግባ» ፕሮጀክት ዳግም እንዲጀመርና ተጠናቆ አገልግሎት እንዲሰጥ ሁኔታዎች ማመቻቸት፤ እንዲሁም ለቀጣይ ከከተማዩቱ መስፋትና ዕድገት ጋር ተያይዞ የውሃ አቅርቦት ከተከዜ የሚገኝበት መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በዘላቂ እንዲፈታ ማድረግ ከተያዙ የረጅም ጊዜ መፍትሔዎች ውስጥ መሆናቸውን ኃላፊው አብራርተዋል።

የውሃ እጥረት እንዲከሰት ምክንያቶች ከሆኑት መካከል በዋናነት የምርት ችግር እንደሆነ የጠቀሱት ዶክተር አሸናፊ፤ የመብራት መቆራረጥ ራሱን የቻለ ዘርፉ ላይ ችግር እየፈጠረ ያለ እንደሆነና የከተማው ውሃ የሚያመርቱ አነስተኛ የውሃ ጉድጓዶች በመበላሸታቸው፤ አስፈላጊ የመለዋወጫ ዕቃዎች ባለመገኘቱ፤ ቢገኝም ተቋሙ ለመግዛት አቅም በማጣቱ ነው ለተጨማሪ ችግሮች እየተዳረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በተጨማሪም በክልሉ ተከስቶ የነበረው ጦርነትም ትላልቅ የውሃ መተላለፊያ ቱቦዎችና ተመሳሳይ ዕቃዎች እንዲበላሹ ምክንያት እንደሆነ አብራርተዋል።

ኃላፊው፤ ችግሩ በጣም ሰፊ ስለሆነ በዋናነት ማኅበረሰቡ የውሃ አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎች እንደ ራሱ በመመልከት እንዲንከባከባቸው መክረዋል። የግብረ ሰናይ ድርጅቶች ከዚህ ቀደም እንደሚያደርጉት አሁንም በተመሳሳይ እገዛቸው ያስፈልገናል ብለዋል።

# ሞያን መሠረት ያደረገ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን የሚደግፍ አዋጅ ለማጽደቅ እየተሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ሞያን መሠረት ያደረገ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን የሚደግፍ አዋጅ ለማጽደቅ እየተሠራ መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዴስክ የሥልጠናና ስርጸት ባለሞያ አቶ እንደገና ፍቃዱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሞያተኞች ባላቸው ሞያ መሠረት አገልግሎቱን መስጠት እንዲችሉ የሚደግፍ አዋጅ ለማጽደቅ እየተሠራ ነው፡፡

እንደ አቶ እንደገና ገለጻ፤ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን በሀብትና በሰው ኃይል በማቀናጀት በፖሊሲ መምራት ያስፈልጋል፤ አገልግሎት ሰጪዎች ከሞያቸው ጋር በተጣጣመ መልኩ አገልግሎቱን አለመስጠት በውጤታማነቱ ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡

የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲ እንዳላቸው የጠቀሱት ባለሞያው፤ በኢትዮጵያም አሁን እየተከናወነ ካለው በተሻለ መልኩ ውጤታማ ማድረግ እንዲቻል የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲ እየተዘጋጀ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከዚህም ውስጥ ትኩረት ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ ሞያን መሠረት ያደረገ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ነው፡፡ በሞያቸው ለማኅበረሰቡ አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ በጎ አድራጊዎች ድረ ገጽ በመጠቀም ያላቸውን ሞያና አድራሻ በድረ ገጹ ላይ እንዲሞሉ በማድረግ እንደሚሠራ አቶ እንደገና ገልጸው፤ ለዚህም የአዋጁ መጽደቅ እየተጠበቀ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ለአብነትም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ባለው የሕክምና ባለሞያ እጥረት ምክንያት በቀላል ሕክምና ሊድኑ የሚችሉ ዜጎች ሕይወታቸውን እያጡ በመሆኑ ይህንንም ለመቀነስ ሞያን መሠረት ያደረገ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን ነው ያነሱት፡፡

አገልግሎት ሰጪዎች በሞያቸው ዘርፍ በመሥራት ሞያቸውን የሚያዳብሩበትና ተቀባዩም ተገቢውን



ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ

**አቶ እንደገና ፍቃዱ**

አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን አሁን ካለበት የተሻለ ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

በጎ ፍቃደኞች አገልግሎቱን በሚሰጡበት ወቅት አደጋ ቢያጋጥማቸው ሊደገፉ የሚችሉበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ወጣቶች በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ እራሳቸውንና ማኅበረሰቡን እንዲጠቅሙ እያደረገ ሲሆን ይህም በወጣቱና በማኅበረሰቡ መካከል ያለውን ቅርበት ለመጨመር ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ትልቅ ትኩረት በመስጠቱ ሁሉም ተቋማት እየተሳተፉበት እንደሚገኝ አንስተው፤ የወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሦስት ሳምንታት በሁሉም አካባቢዎች ተካሂዶ የተለያየ ቋንቋና ባህል ባላቸው ወጣቶች መካከል ማኅበራዊ መስተጋብርን ማጠናከር መቻሉን አውስተዋል፡፡

አቶ እንደገና እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ከሰኔ 16/2015 ዓ.ም ጀምሮ ከዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደቤተሰቦቻቸው የሚመጡ ወጣቶችን ማዕከል በማድረግ ወሰን ተሻጋሪና ለሦስት ወራት የሚቆይ የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመባል በሁለት ዓይነት መልኩ እየተከናወነ ሲሆን ይህም እስከ መስከረም 30/2016 ዓ.ም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በዚህም ከ20 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችን በማሳተፍ 51 ሚሊዮን የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ በማድረግ ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ለማትረፍ እንደታቀደ አስታውሰው፤ እስካሁን ባለው አፈጻጸም አመርቂ ውጤት እየተመዘገበ በመሆኑ በቀሩት ጊዜያት እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል የተሻለ አፈጻጸም እንደሚመዘገብ አቶ እንደገና ተናግረዋል፡፡

# ትውልድን

## የተመረኮዘው የሀገር ግንባታ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ ሲሉ ይተርታሉ አበው። እንዲህ ያለው ቃል ለዚህ ጉዳይ ተገቢ አማርኛ ነው። ሀገርን ለመገንባት ትውልድን ማብቃት አቻ የሌለው ተግባር ነው። ትውልድን ብቁ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም። አሁን ላይ ትናንት አብነት ይደረጋል። ዛሬንም እንደ መልካም ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል። ትውልድ እንደ ሻማ ነው። ከተንከባከቡት ቀልጦ ይበራል፤ ካልሆነ ጥቅም ሳይሰጥ ይቀልጣል። ትውልድን መገንባት ለእከሌ ተብሎ የተጣለ ግዴታ አይደለም። የሁሉም ኃላፊነት ነው።

ትውልድ ብቁ፣ ጠንካራ የሥነ ልቦና ውቅር ያለው መሆን አለበት። በሥነ-ምግባር ሊታነጽም ይገባዋል። ማኅበራዊ እሴቶችን ያዳበረ አርቆ አሳቢ ትውልድ ለማፍራት የቤት ሥራዎች አይታጡም። ግለሰቦች፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ ቤተ-እምነቶች ኃላፊነት በመውሰድ ረገድ ግንባር ቀደም ናቸው።

ሀገራት መለያያ መንገድ አያጡም። ሀብት፣ ቴክኖሎጂ፣ እውቀት እንዲሁም ባህልና እሴት አንዱን ከሌላው ይለያሉ። እነዚሁ ሀገራት ልዩነቶችን ለማጥበብ ጎንበስ ቀና ሲሉ መመልከት የተለመደ ነገር ነው። ይህም መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም ያስችላል። እዚህ ላይ የዳያስፖራው ያለው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጉዳዩን በሚመለከት ጠይቋል። መላሹ አቶ ደመቀ ነጋሳ ይባላሉ። በአውሮፓ ኔዘርላንድ ለብዙ ዓመት ኖረዋል። የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት ናቸው። ስለትውልድ ግንባታ የልባቸውን አውግተዋል። ኢትዮጵያውያኑ የውጭ ነዋሪዎች ትውልድን በመገንባት ሂደት ውስጥ የማይተካ ሚና አላቸው።

በሀገሪቱ ዘላቂ ልማት ማምጣት ላይ ዳያስፖራው ስላለው አስተዋፅኦ በአቶ ደመቀ ተጠቅሷል። እውቀትን፣ ልምድን፣ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ኢኮኖሚን ከመደገፍና የሀገሪቱን ዲፕሎማሲ ማሳደግ ላይም ሚናቸው ከቁጥር በላይ ነው ባይ ናቸው። ዳያስፖራው የሀገሪቱን ባህል፣ እሴት ለተቀረው የዓለም ክፍል ያስተዋውቃል። ይህን ለማድረግ ጠቃሚ የሆኑ አዲስ አሠራሮችን ወደ ሀገራቸው ማስተላለፍ ተገቢ ነው።

ሀገርን በዘላቂነት ለመገንባት ትውልድ ላይ መሥራት የማይዘነጋ ቀዳሚ ተግባር ነው። ዳያስፖራው በቴክኖሎጂ ሊያለማ ይገባዋል። በመሠረተ ልማት ላይም መሳተፍ አለበት። አቶ ደመቀ በኢንቨስትመንትና ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ቢሳተፉ መልካምነቱን ገልጸዋል። ለኢትዮጵያውያኑ ትውልድን መገንባት ጎን ለጎን ሌሎችም ሥራ አሏቸሁ ብለዋል። ለልጆቻቸው ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና ቋንቋቸውን ማሳወቅ አለባቸው።

ብርሃኑ ገረመ (ዶ/ር) ቀጣይ አስተያየት ሰጪ ናቸው። አውሮፓ ነዋሪ ናቸው። የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ምን ይጠበቅብናል ለሚለው ምላሽ ሰጥተዋል። ትውልዱ ላይ ስለሚከወኑ ተግባራት አስፈላጊነት ገልጸዋል። የዳያስፖራው ተሳትፎ መጠነከር መቻል አለበት ብለዋል።

ዳያስፖራዎች በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ ተሳታፊ ናቸው። የትምህርትና የምርምር ተቋማት ላይ ይገኛሉ። ይህም በትምህርት ላይ ሰፊ ተግባር ለማከናወን አቅም ይፈጥራል። በዚህ ብቻ መቆም አያስፈልግም። ቀጣይ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል። ያለውን ተሞክሮ ማካፈል ይገባል። ዴሞክራሲ ማጎልበት ሂደት ላይ ሚናው ጉልህ ነው። በቴክኖሎጂ ሽግግርና መልካም አስተዳደር ግንባታም ላይ ሥራው ቀላል አይባልም። በተለያዩ ዘርፎች ያለ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ይመክራሉ።

ዜና

# በክልሉ ከ25 ሺህ በላይ ነዋሪዎች በጎርፍ አደጋ ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለዋል

## • ከ36 ሺህ በላይ የሚሆኑት ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል





**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ባጋጠመው የጎርፍ አደጋ ከ25 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ከመኖሪያ ቀያቸው ሲፈናቀሉ ከ36 ሺህ በላይ የሚሆኑት ላይ ደግሞ ጉዳት መድረሱን የክልሉ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የጋምቤላ ክልል አደጋ ስጋት ሥራ አመራር አገልግሎት ተወካይ ዳይሬክተር አቶ ሉል ጎኘ ባንጎት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ባጋጠመው ጎርፍ ዜጎች ተፈናቅለዋል ንብረት ወድሟል። በዚህም የጎርፍ መጥለቅለቅ ከደረሰባቸው ዘጠኝ ወረዳዎችና ጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ውስጥ 25 ሺህ 140 ነዋሪዎች ከመኖሪያ ቀያቸው ሲፈናቀሉ 36 ሺህ 129 የሚሆኑት ላይ ደግሞ ጉዳት ደርሷል፡፡

ተፈናቃዮቹ በትምህርት ቤቶችና በቤተ እምነት ስፍራዎች ተጠልለው እንደሚገኙ ያነሱት ተወካይ ዳይሬክተሩ ችግሩን ለመቅረፍ እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች መካከልም ለተፈናቃዮቹ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር አፋጣኝ ድጋፍ የሚደርስበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን አንስተዋል፡፡

እንደ አቶ ሉል ጎኘ ገለጻ፤ በጋምቤላ ክልል የጎርፍ አደጋ በክረምት ወቅት የሚፈጠር የተለመደ ክስተት ነው። በጋምቤላ ከተማ ስር በሚገኙ አራት ቀበሌዎች ዜጎች ተፈናቅለው በተለያዩ ስፍራዎች የተጠለሉ ሲሆን ይህ መሆኑም በክልሉ ያለውን የሰብአዊ ሁኔታ የሚያባብስ ክስተት ነው፡፡

የዜጎች መፈናቀል እና ጉዳት ላይ መውደቅ ዜጎች ሕይወታቸውን በአግባቡ እንዳይመሩ እንቅፋት በመሆን እንደ ምግብ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ያሉ ፍላጎቶችን በመጨመር ሰብአዊ ቀውስ ያስከትላል ብለዋል፡፡

በክልሉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በመስተዋሉ እንደ ባሮ እና ጊሎ ያሉ ዋና ዋና ወንዞች ሞልተው በመፍሰሳቸው ምክንያት በአኙዋክ፣ ኑዌር ዞኖች እና በኢታንግ ልዩ ወረዳ የጎርፍ መጥለቅለቁ ሊያጋጥም ችሏል ነው ያሉት።

ጎርፉ በጤና ኬላ እና ጤና ጣቢያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ላይ ሲሆን ለምሳሌ በኢታንግ ጤና ጣቢያ ላይ ጫና በማሳደሩ አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች እንደሆነ አቶ ሉል ጎኘ ጠቁመዋል።



# የአደባባይ በዓላትን ይበልጥ በማስተዋወቅ

## ለቱሪዝም ገቢ ያላቸውን ሚና ማሳደግ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ በማስተዋወቅ ለቱሪዝም ገቢ ያላቸውን ሚና ማሳደግ እንደሚገባ የቱሪዝም ባለሙያዎች ገለጹ፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያ አቶ አሸናፊ ደስታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመስከረም ወር በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከናወኑ የአደባባይ በዓላት ለቱሪዝም ገቢው ዕድገት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በኢትዮጵያ የተለያየ ሃይማኖትና ባህል የሚንጸባርቅባቸው በርካታ የአደባባይ በዓላት እንደሚከበሩ አንስተው፤ በአደባባይ በዓላቱ የኢትዮጵያውያን ሃይማኖት፣ ባህልና ትውፊት በስፋት የሚንጸባረቅበት በመሆኑ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎችን መሳብ ይቻላል ብለዋል።

በኮቪድ ወረርሽኝና በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት ወደኢትዮጵያ ይመጡ የነበሩ ቱሪስቶች ቁጥር ባለፉት ዓመታት የመቀነስ አዝማሚያ መታየቱን ጠቁመው፤ አሁን ላይ የሚከናወኑ የአደባባይ በዓላትን ይበልጥ በማስተዋወቅ ቱሪዝሙን ማነቃቃት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ አሸናፊ ገለጻ፣ በመስከረም ወር በኢትዮጵያ የሚከበሩትን የመስቀል ደመራ፣ ኢሬቻ፣ ያሆዴ፣ መሰላ፣ ማሽቃሮ፣ ጊፋታ ጋሪወሮ፣ ሄቦ፣ ዮ መስቀላ፣ ጋዜና ሌሎች የአደባባይ በዓላት ላይ በርካታ ቱሪስቶችን መሳብ ይቻላል።

የቱሪስቶችን ፍሰት በማሳደግ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታን ማጎልበት የሚቻልበትን ዕድል ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል።

በዓላቱ ከቱሪዝም ዕድገት በተጨማሪ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን በማጎልበት አንድነትን ለማጠናከር እንደሚረዱ ተናግረዋል።

የአደባባይ በዓላቱ በሚከበሩበት አካባቢዎች የበዓሉ ተሳታፊዎች የሚደምቁባቸውን አልባሳት፣ ጌጣጌጥ እና የአካባቢውን ባህላዊ ምግቦች አዘጋጅቶ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባም አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላትን ወቅቱን ጠብቆ ከማክበር ባለፈ በቅርስነት ለመጠበቅ፣ ለሌሎች ሀገራት ለማስተዋወቅና ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

አቶ አሸናፊ እንዳመላከቱት፤ በአደባባይ በዓላት ላይ የሚታዩት ጭፈራዎችና ዘፈኖች ለኪነጥበብ ዘርፉ ዕድገትና ባህልን ለማስተዋወቅ ይረዳሉ።

ሌላኛው የቱሪዝም ባለሙያ አቶ ቃለአብ በላቸው በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የአደባባይ በዓላት የማኅበረሰብ ባህላዊ መገለጫዎች ናቸው።

በዓላቱን የቱሪዝም ገቢ ምንጭነት በመጠቀም የውጭ ምንዛሬ ግንታችንን ማስፋት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያን የአደባባይ በዓላት በዓለም አቀፍ ሚዲያዎችና ድረ-ገጾች በቀጥታ ማስተላለፍ የሚቻልበትን ዕድል በመፍጠር የተለያዩ ቱሪስቶችን መሳብ እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

አደባባይ በዓላት ሲከበሩ የኢትዮጵያን ሃይማኖት፣ ባህልና ትውፊት በሚያሳይ መልኩ መሆን አለበት ያሉት አቶ ቃለአብ፤ አንዱ ብሔር የሌላውን ባህል፣ ዕምነት፣ አስተሳሰብና ማንነት በማክበር በጋራ ማክበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን የአደባባይ በዓላት አከባበር ለመጎብኘት ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን በአግባቡ ተቀብሎ በማስተናገድ የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ማድረግና የቱሪዝም የገቢውን ማሳደግ እንደሚገባም አመላክተዋል።

# በዓላት

# ለአብሮነትና ለጠንካራ መስተጋብር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

በኢትዮጵያ በርከት ያሉ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላት ይከበራሉ፡፡ ዘንድሮም በመስከረም ወር የመውሊድ፣ የደመራ፣ የመስቀል እና ኢሬቻ በዓላት በልዩ ድባብ ይከበራሉ፡፡ በተለይ በደቡብ የሀገራችን ክፍል የሚከበሩ የዘመን መለወጫዎች በጉጉት የሚጠበቁ በዓላት ናቸው፡፡

ኢትዮጵያውያን ለበዓላት ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ የበዓላቱ ድምቀት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ወዳጅ፣ የዘመድ አዝማድና ጎረቤት አብሮ የሚከበርበት ነው፡፡ መጠያየቁና እንኳን አደረሳችሁ መባባሉ ታዲያ በአንድ ቤተ እምነት ስር ባሉ ብቻ ሳይሆን የተለያየ እምነት ተከታይ በሆኑ ሰዎች መካከል ጭምር የሚከናወን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በዓላት በሕዝቦች መስተጋብር መጠናከር እና አብሮነት መጎልበት የማይተካ ሚና እንዳለው የሚያመላክት ነው ይላሉ የዘርፉ ምሁራን፡፡

ይህን ጠንካራ መስተጋብር እና አብሮነት እንዴት ለሀገር ሰላም መስፈንና አብሮነት መጠናከር እንጠቀመው የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በበዓላት አከባበር ወቅት የሚስተዋሉ መልካም እሴቶች ኅብረተሰቡን ከማስተሳሰር አንጻር ያለው እንድምታ እንዴት ይገለጻል? በቀጣይነትስ በምን መልኩ እንጠቀምባቸው በሚለው ላይ የዘርፉን ምሁራን አነጋግሯል፡፡

የሕገ መንግሥትና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኃይለኢየሱስ ታዬ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ የሃይማኖት፣ የባህልና የሌሎችም ጉዳዮች ብዝሃነት ያለባት ሀገር ናት፡፡ ይህን ብዝሃነት በትክክል ከተጠቀምንበት ለሀገራችን ትልቅ ዕድል ይዞ የሚመጣ እምቅ ሀብት ነው፡፡

ብዝሃነት ያለበት ሀገር ውስጥ ተቻችሎ፣ ተከባብሮ መኖርና ሁሉንም የራስ አድርጎ መውሰድ እንደሚጠይቅ የሚጠቅሱት ዶክተር ኃይለኢየሱስ፤ ማኅበረሰቡ ብዝሃነት ስጋት ሳይሆን ሀብት መሆኑን በመገንዘቡ ለዘመናት የሌሎችን በዓላት እንደ ራሱ ተቀብሎ በዓላትን በጋራ እያከበረ ዘልቋል፡፡ ይህም አንዱን ማኅበረሰብ ከሌላው ጋር ያለው ቁርኝት ጠንካራ እንዲሆን ማድረጉን ያስረዳሉ፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስብስብና መጠላለፍ የበዛበት ነው፡፡ ማኅበረሰቡ የገነባው መልካም እሴት ግን አብሮነታችን እንዳይበጠስና መስተጋብራችን እንዲጠናከር አድርጓል፡፡ ይህን ጠንካራ ትስስር በመፍጠር በኩል ደግሞ በዓላት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ መልካም እሴት ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍና የሕዝቦች አንድነት እንዲጠናከር መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮች በዋናነት ከፖለቲካው የሚመነጩ መሆናቸውን የሚጠቅሱት ዶክተር ኃይለኢየሱስ፤ ለማኅበረሰቡ የሚያስቡ መስለው በሕዝቦች መካከል መቃቃር የሚፈጥሩ አካላት በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ የኢትዮጵያውያን ዕጣፈንታ ተከባብሮና ተግባብቶ መኖር ስለሆነ ማኅበረሰቡ የሚከሰቱ ችግሮችን በዝምታ ከማየት ወጥቶ አብሮነቱ ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ አካላትን መቃወም ይኖርበታል ነው ያሉት፡፡

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህሩ አቶ አንዷለም አሰፋ በበኩላቸው፤ በዓላት የመሰባሰብ፣ የአንድነትና የተጣሉ የሚታረቁበት ነው፡፡ ይህም በማኅበረሰቡ መካከል የመከባበር፣ የመተባበርና የመቻቻል እሴት እንዲጎለብት አድርጓል፡፡

በበዓላት ወቅት የሚስተዋሉ አብሮነትና የመተባበር መንፈስን የየዕለት ተግባራችን ማድረግ እንደሚገባ የሚጠቁሙት ምሁሩ፤ በየአካባቢው ችግሮችን ለመቅረፍ፣ የተጣላን ለማስታረቅና ለመተባበር የሚውሉ መስተጋብሮችን እንደመነሻ በመውሰድ በሀገር ደረጃ መተግበር ይጠበቅብናል ይላሉ፡፡

በተለይ በፖለቲካው መድረክ ዋና ተዋናይ የሆኑ አካላት የማኅበረሰቡ መልካም እሴቶች የሆኑትን አብሮ የመኖር፣ መፈቃቀርና መቻቻልን በፖለቲካው ላይ ቢተገብሩት እንደ ሀገር ያጋጠሙንን ፈተናዎች መሻገር እንደሚያስችል አመልክተዋል፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ በዓላትን በመሰባሰብ ማክበራችን በማኅበረሰቡ መካከል ጠንካራ መስተጋብርና ግንኙነት እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በበዓላት ወቅት ላለመለያየት ችግሮች ቢኖሩ እንኳን ተነጋግሮ የመፍታትና የመታረቅ ትልቅ ልምድ አለ፡፡ በመሆኑም ከመገፋፋትና ከመነታረክ ወጥተን በሰላም እንድንኖር ፖለቲከኞች የማኅበረሰቡን መልካም እሴቶች በፖለቲካው መድረክ መጠቀም ይኖርብናል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኮሚሽኑ ተስፋ ያደረግናቸውን ብሩህ ነገዎች ተጨባጭ ለማድረግ ትልቁ አቅማችን ነው!

ሀገራችን በየዘመኑ በውስጣዊና ውጪያዊ ችግሮች በብዙ ከተፈተኑ ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ናት። ከዚህ የተነሳም እንደ ሕዝብ ዜጎቿ መሆን የሚፈልጉትን መሆን አቅቷቸው ዘመናት ተቆጥረዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃም የኋላ ቀርነትና የድህነት ማሳያ ለመሆን የተገደዱበት እውነታ የአደባባይ ምስጢር ነው ።

አንዳንዶቹ ችግሮች የተፈቱበት ሆነ፤ የተያዙበት መንገድ ጤነኛ ባለመሆኑ የተነሳም ዘመን ተሻግረው የተጨማሪ ችግር ምንጭ ሆነዋል፤ ላልተገባና የተፋለሰ የታሪክ ትርክት ምክንያት በመሆንም ሀገርና ሕዝብን ያልተገባ ዋጋ አስከፍለዋል፤ ዛሬም እያስከፈሉ ነው።

ከዚህም ባሻገር የትውልዶችን አእምሮ ባልተገባ የጥፋት መንገድ በመምራት ትውልዱ የራሱን መሻት እንዳይኖር፣ ለሀገሩ የሚያስበውን በጎ ሃሳብ ባለው እውቀት እና ጉልበት ሳይቆጥብ ተግባራዊ እንዳያደርግ አድርጎታል። በራሱና በሀገሩ ጉዳይ ባይተዋር እንዲሆን አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥም ከትቶታል።

ከዚያም ባለፈ በዘመናት እንደ ሕዝብ የቀደሙት አባቶቹና አያቶቹ ሀገርን እንደ ሀገር ጠብቀው ካቆዩባቸው ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ እና ባህላዊ እሴቶች እየተጣላ፤ የሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች የጥፋት መጥመድ ሰለባ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ ተስፋ ከመሆን ይልቅ፤ ስጋት የሚሆንበት የተደጋገሙ ታሪካዊ ክስተቶች ተፈጥረዋል።

በዚህም እንደ ሀገር ብዙ ዋጋዎችን ለመክፈል ተገደናል፡፡ ጦርነት፣ ሞት ፣ ስደት ፣ መፈናቀል እና ረሀብ የሕዝባችን የየዘመኑ መገለጫ መሆን ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። በየዘመኑ በብዙ ጣር ትውልዶች ያማጧቸው የብሩህ ቀናት ምጦች ጨንግፈዋል፡፡ የብሔራዊ ኀዘንና ቁዘማ ምንጭ ሆነዋል።

እነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ያለማግኘታቸው እውነታ ደግሞ ፤ በየዘመኑ ለሚነሱ የፖለቲካ ቆማሪዎች / ነጋዴዎች አዋጭ እና ርካሽ የፖለቲካ ሸቀጥ ሆኖላቸዋል፡፡ በተለያዩ አዳዲስ የጥፋት ትርክቶች አቅም እየገዙ ሀገርን እንደ ሀገር የህልውና ስጋት ውስጥ መክተት ችለዋል።

ይህ ትውልድም እንደቀደሙት ትውልዶች ሁሉ እነዚህ ችግሮች አሁንም ድረስ በሚነገረው የጥፋት ትርክት ልክ ከፍያለ ዋጋ ስለመክፈሉም ሆነ፣ እየከፈለ ስለመሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ችግሩም ዛሬ ላይ የሀገራችን የሕዝባችን የሰላም እጦት ዋንኛ ምክንያት እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በቀደመው የፖለቲካ ሥርዓት እነዚህ ችግሮች ከአቅማቸውና ከአውዳቸው፣ ከዚያም ባለፈ ከዘመኑ እሳቤ ባፈነገጠ መንገድ፤ የፖለቲካ አጀንዳ ተደርገው መወሰዳቸው፤ የሀገርን ህልውና በየትኛውም ሰዓት አደጋ ውስጥ መክተት የሚያስችል አቅም እንዲይዙ አድርጓቸዋል።

ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ ሕዝባችን እንደ ሕዝብ የተነቃቃበትን የለውጥ አስተሳሰብና ለለውጡ ያለውን ቁርጠኝነት፤ እንደቀደሙት ዘመናት የለውጥ ትርክት ተቃርኖ ውስጥ በመክተት፣ ለማቀዛቀዝ ለተለያዩ ጸረ-ለውጥ ኃይሎች መገልገያ ተደርገውም ነበር።

ሀገርን እና ትውልዶችን በየዘመናት ብዙ ዋጋ ሲያስከፍሉ ከመጡ ከነዚህ ችግሮች ለመታደግ ይህ ትውልድ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት ይታመናል። ይህንን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣትም የተሻለ ግንዛቤ፤ ተጨባጭ ተሞክሮ እና መልካም ዕድሎች አሉት።

ከነዚህ ዕድሎች መካከል ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽን አንዱ ነው። ኮሚሽኑ እነዚህን ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ችግሮችን በንግግርና በውይይት ለመፍታት እየሄደበት ያለው መንገድ፤ ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ ከማፈላለግ ባለፈ፤ ሀገርን እንደ ሀገር ከግጭት አዙሪት ማውጣት የሚያስችል ትልቅ አቅም ነው።

ከችግሮቹ በስተጀርባ ያሉ የጥፋት ትርክቶችን በማጥራት፤ ለችግሮቹ ዘመኑን የሚዋጅ መፍትሔ ለማፈላለግ ዕድል የሚሰጥ፤ በታሪክ ትርክቶች ልዩነቶችን ከማስፋት ይልቅ፤ ከታሪክ ተምረን አሁናችንን፤ ተስፋ ያደረግናቸውን ብሩህ ነገዎች ተጨባጭ ለማድረግ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚረዳን ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዛሬ ከትናንት እንዲሻል

ታምራት ተስፋዬ

የአይሁድ ዝርያና የደች ዜግነት ያለው ታዋቂው የፍልስፍልና ጠቢብ ባሩች ስፒኖዛ Baruch Spinoza « If you want the present to be different from the past, study the past/ዛሬ ከትናንቱ የተሻለ እንዲሆን ከፈለግክ የትናንቱን በሚገባ አጢነው/»የሚል አባባል አለው፡፡ ይህን አባባል በተለይ አዲስ አመትን ስንጀምር ይበልጥ ትርጉም ይሰጣል፡፡ ወደ አዲስ አመት ስንሸጋገር ካለፈው ልምድና ተግባራችን ትምህርት መቅሰም እንደሚገባን ያስገነዝባል፡፡

ይሁንና አንዳንዶች በአሮጌ አመት የሠሩትን ስህተት በአዲሱ አመትም ደግመው ሲሠሩ ራሳቸውን ያገኙታል። ይህም ያለፈውን ልምዳቸውን የመለየትና ለመፍትሔ የመራመድ ፍላጎትም ሆነ ልምድ ስለሌላቸው የሚከሰት ስለመሆኑ እርግጥ ነው፡፡

ዛሬ ላይ ሆኖ የትናንት ተግባር ምን ጠቀመን? ስህተቱስት ምን አስተማረን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትክክለኛውን መልስ ፈልጎ ማግኘት የቻለ ግን ከዚህ ቀደም የጨበጠውን እሳት ዳግም እንደማይጨብጠው የሚያጠራጥር አይደለም፡፡፡

የዘመን በዘመን የጊዜ በጊዜ መተካት የማያቋርጥ ሂደት ቢሆንም አዲስ ዓመት ሰው ከራሱ ጋር ይታረቅ ዘንድ እቅዱ ከግቡ እንዲስማማ ውጫዊና ውስጣዊ ሕይወቱ እንዲጣጣም ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ አዲስ ዓመት የሰው ልጅ ራሱን የሚያሻሽልበት ያለፈውን ሕይወቱን ገምግሞ ደካማውን ሸሮ ጠንካራውን ይዞ እንዲቀጥልበት ለራሱ የፈጠረው የቀን ቀጠሮ ነው፡፡

አዲስ አመትም ራስን ለመለወጥ፣ አስተሳሰብን ለማደስ፣ አኗኗርን ለማስተካከል፣ ለማሰብና ለማሰላሰል ዕድል ይሰጣል፡፡ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ሰው ባሰመረው የጊዜ ድንበር ለአዲስ አመት ሁሌም አዲስ ያስባል፡፡

ኢትዮጵያውያንም 2015 ዓ.ም አሮጌ ብለው ሸኝተው አዲሱን 2016 ዓ.ም ተቀብለዋል፡፡ አዲስ አመትም በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ አዲስ ቃል የሚገቡበት ዕለት ነው፡፡ ሁሉም በየፊናው መጪው ጊዜ መልካም እንዲሆን፤ ኑሮው እንዲሳካ ጎጀው እንዲሞላ፣ መንፈሱ እንዲረካ፣ አዕምሮው እንዲሰላ፣ ነፍስያው እንዲጠግብ፣ የውስጡም የውጭውም ሕይወቱ እንዲያምር ያቅዳል፡፡

ለአብዛኞቻችን ኢትዮጵያውያንም እውነተኛው የአዲስ ዓመት ትርጉሙም አዲስ ሰውነት፣ አዲስ አስተሳሰብ፣ አዲስ ለውጥ፣ አዲስ የሕይወት መንገድ የሚበጅበት፣ ለራሳችን ቀና አስተሳሰብ የምንቀይስበት በአጠቃላይ አዲስ የምንሆንበት የአዲስነት የጅማሮ ቀን ነው፡፡

አዲስነት የትናንቱን ድካም፤ ያለፈውን አጉል ልማድ መድገም ሳይሆን አዲሱን ኑሮ በአዲስ ሰውነት፣ በሰለጠነ አስተሳሰብና በቀናነት መጀመር ነው፡፡ አዲስነት በግንዛቤ መበልጸግ፣ በጥበብ መጎልመስ፣ ራስን በመቆጣጠር መርቀቅ ጭምር ነው፡፡

አመቱ አዲስ እንዲሆን ደግሞ አዲስ ሰው መሆንን የግድ ይላል፡፡ አዲስን ወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ እንደማይጨምሩት እና አዲሱና አሮጌው እንደማይስማሙ ሁሉ ሰው በአዲስነት ካልተቀበለው አዲስ አመትም የቁጥር ለውጥ ብቻ ይሆናል፡፡

ይሁንና በዘመን ሂደት በትውልድ ቅብብል የማይጠቅምን አስተሳሰብን ማራመድ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ሕዝብ ጉዳቱ ግልፅ ነው፡፡ አንድ ከማድረግ ይልቅ የሚነጣጥል፤ መሰብሰብን ትቶ የሚበትን፣ ከማዋሃድ ይልቅ የሚለያይ አስተሳሰብን ማራመድ ኪሳራ እንጂ ትርፍም የለውም።

እንግማ መታወቅ ያለበት ወሳኝ ጉዳይ ቢኖር ማሰብ መቻል ልዩ ፀጋ ነው። መልካምን ሃሳብን መርጦ መተግበር ደግሞ ሰው በራሱ ላይ የሚያመጣው በረከት ነው። ማንም ለሆዱ የሚስማማውን ምግብ እንደሚመርጠው ሁሉ ለአዕምሮውም የሚመጥን ሃሳብን መመገብ ራስን መጥቀም ነው።

ንፁህ ምግብ ሰውን ከበሽታ እንደሚከላከለው ሁሉ ንጹህና መልካም ሃሳብም ሰውን አፍራሽ ተልዕኮ ካለው ተግባር ያቅበዋል። ሰው ሃሳቡን እያበጠረ ገለባ ሃሳቡን የሚያስወጣበትና ጠቃሚውንና ፍሬ ሃሳቡን የሚያስቀርበት የሕሊና ወንፊት መሥራት ይገባዋል። ሃሳብ እንደስንዴ እንክርዳድ ካልተጣራ ንጹሁንም ሃሳብ ያበላሻል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ትናንት በሃሳብ ቀድመን ከፍ ከፍ እንዳላልን ዛሬ አዲስ ሃሳብ መሥራት፣ ሃሳቡን ማርቀቅ፣ ሃሳቡን ማጎልመስ፣ ሃሳቡን በተሻለ ሃሳብ መጣል፣ ሃሳቡን በሃሳብ ማድመቅ የሚያስችል ባህል ጠፍቶብናል። ትናንትም ሆነ ዛሬ እየተመላለሰ የሚደቁሰንና አዙሪት ሆኖብን ወደፊት አላንቀሳቅስ ያለን ችግራችንን በአስተሳሰብ ልዕልና ተነጋግረንና ተወያይተን ፍቱን የሆነ መፍትሔ ማስቀመጥ አለመቻላችን ሆኖም ይታያል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ያለፈው ዓመት ደስታና ኀዘን ተስፋና ፍርሀት ድልና ትግል የተፈራረቁበት እንደነበር ይታወሳል፡፡ የምንሰማውና የምንናገረው የምንፈልገውን ብቻ ሆኖ በጥቂቱ አውቆ በብዛት መደምደም፣በከፊል ሰምቶ በሙሉ መፍረድ፣ መርጦ በመመልከትና በመስማት ሳይመርጡ ማውገዝ የሁላችንም መገለጫ ሆኖም ታይቷል፡፡

ይህን ታሪክ በአዲስ አመት መለወጥ ይኖርብናል። ኢትዮጵያውያን በአዲሱ አመት ካለፈው ተምረን መጪውን ለማሳመር በተለይም ሀገር ሠላም እንድትሆን ካሳለፍናቸውም መልካም ሆነ እኩይ ታሪኮች ተምረን መጪውን ለማሳመር ማድረግ ያለብን ብዙ ነው፡፡

ኢትዮጵያችን በአዲስ አመት አዲስ አስተሳሰብ ያለው ዜጋን ትፈልጋለች፡፡ የሚከሳት እንጂ የሚከሳት አያስፈልጋትም፡፡ ዘመን የሚዋጅ፣ ትውልድን እንደ አዲስ የሚቀርፅ ትውልድ ትባጃለች፡፡ ትንሳኤዋን የሚሻ፣ ወደ ኋላ የሚጎትትና የማይጠቅም አስተሳሰብ በአዲስና በተሻለ አስተሳሰብ መለወጥ የሚችል ዜጋን ትናፍቃለች፡፡ ሊገነባ፣ ትውልድ ከፍ ከፍ ሊያደርግ የሚችል አስተሳሰብ ትሻለች።

በአዲስ ዓመት ለመናቆር ሳይሆን ለመፋቀር ቦታ እንስጥ፡፡ ፀጉር ከመንጨት፣ ሃሳብ ማመንጨት እናስቀድም፡፡ ከመቆላለፍ መተላለፍን፣ ከመተናነቅ፣ መደናነቅን እንምረጥ፡፡ የአምናውን ዕዳ አንውረስ። የአምናውን ክፋት አንጨርስ፡፡ አዲስ ጎዳና ይተለም። አዳዲስ ፈትል ይቀለም፡፡ ተከፋፍሎ መፍረስ ይብቃ፡፡ ለቆጡ ተንጠራርተን የብብቱ አያምልጠን፡፡

የእብደቱ መንገድ ቁልቁለቱ፣ በዘር ሀረግ መለቃቀም፣ በእምነት ጥላ መጠቃቀም ይብቃን፡፡ በሰውነት እንከባበር። ማድላት ማግለል እንቅበር፡፡ ቅን እናስብ። ቅን እንናገር፡፡ አፍና ልባችን አንድ ይሁን፡፡ ወጥመዱን ሁሉ እንበጥስ፡፡ ተንኮሉን ሁሉ እናፍርስ፡፡

በአዲሱ አመት በአስተሳሰብ ለውጥ «እኛ እነሱ»፣ «የእኛና የእነርሱ» የሚል ዘረኛ ቀይ የጎጥ መስመር ከማጋደም እንቆጠብ፡፡ በብሔር መነፅር ተሸፍነን «እንዲህ ነን» ስላልን «እንዲያ» እንደማንሆን እንገንዘብ። የባንዲራ ክብር ይታየን፡፡ በጎጥና መንደር የጠበበ ሰው አስፍቶ ማሰብ ይሳነዋልና ከጎጥ አስተሳሰብ እንገንጠል፡፡

ምግባርና ተግባር የጎደለን፣ የሚጨበጥና የሚያዝ የሌለን አንሁን፡፡ ኀሊና ያድሰን፡፡ ሰውነት ይመልሰን። ሃይማኖት ይፈውሰን፡፡ የሀገር ፍቅር ድምጽ ይሠማን። ሁሉንም ወቃሽ ከመሆን እንቆጠብ፡፡ «ተበድያለሁ» ከሚል በደል ቆጣሪነት እንፋታ፡፡ ከተገፊነት ተረክ እንላቀቅ፡፡ከሚያነቃቅፈን ይልቅ የሚያስተቃቅፈንን እንምረጥ፡፡ ቃልና ተግባራችን ይመጣጠን፡፡

በአዲስ አመት ባለፈውና ባሳለፍነው አጉል ጊዜ መቆጨትን ማቆም እና ለወደፊቱ መሻልን ማሰብ ልንጀምር ይገባል፡፡ ከማፍረስ ይልቅ መካብ ሊቀለን፣ ይገባል። ኋላቀርነት ሊማርከን፣ መጥፎ ታሪክ ሊጎትተን፣ ዘመን ሊያድሰን፣ ክፉ ትናንት ሊቀይረን አይገባም። ከመጥበብ መስፋትን እንምረጥ፡፡ ለሕዝብ የማይበጅ የሴራ ፖለቲካ መጎንጎን ማቆም አለብን፡፡

በአዲስ አመት በዚህ አስተሳሰብ ለመቃኘና አስተሳሰቡን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ለዚህ የሚመጥን ጭንቅላት መፍጠር ግድ ይለናል። አስተዋይ ጭንቅላት አንድም ከመጽሐፍ ማሕፀን በንባብ ምጥ የሚወለድ፤ አንድም ትናንትን በማስተዋልና የኋላ ታሪክን ተጠቅሞ በበጎ እሳቤ በመለወጥ እውን እንደሚሆን ልንረዳም ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ ከቻልን የተሻለችና በሁሉም መስኮች የተሳካላት ኢትዮጵያን ማየት ህልም አይሆንብንም፡፡

አዲሱ አመት ምንም ልንለውጠው ከማንችለው ትናንት ይልቅ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ልናደርግበት በምንችልበት ነገ ላይ እንረባረብ፡፡ ስለትናንትና አበክረን ስንናገር ዛሬና ነገ እንዳያመልጡን እንንቃ፡፡ መጪው ዓመት ያለፈውን እያስታወስንና እያወሳን የምንጋጭበት ሳይሆን መጪውን እያለምንና እየተለምን በአንድነት በፍቅር ተደምረን የምንፈስበት ጨርሶ የመጀመር ዓመት ይሁንልን፡፡

# በአዲስ አበባ 20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

## - በምርቃቱ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ማዕድ አጋርተዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ 20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጋር በመሆን በማዕከሉ ለአረጋውያን ማዕድ አጋርተዋል።

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ትናንት በተከናወነው የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ ለከተማችን ነዋሪዎች ተጨማሪ የአዲስ ዓመት ስጦታ ይሆን ዘንድ 20ኛውን የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንት አገልግሎት አስጀምረዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩንም በተጠቃሚዎቹ ስም ላመሰግን እወዳለሁ ብለዋል።

የምገባ ማዕከሉ ከ500 በላይ ለሚሆኑ የአካባቢው አቅመ ደካማ ነዋሪዎች በቀን አንድ ጊዜ የተመጣጠነ ምግብ የሚያቀርብ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በአጠቃላይ በከተማችን ባሉ 20 የምገባ ማዕከላት ከ35 ሺህ በላይ ወገኖቻችን አገልግሎት እያገኙ ነው ብለዋል።

«በርካታ ሜጋ ፕሮጀክቶችን አስመርቀን ሥራ አስጀምረናል። ነገር ግን የፕሮጀክቶቻችን ሁሉ ሜጋ ፕሮጀክት የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት ናቸው» ሲሉም ተናግረዋል።

በ2013 ዓመተ ምህረት የመጀመሪያውን የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ሥራ ማስጀመራቸውን ያነሱት ከንቲባ አዳነች፤ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ኢትዮ ሴራሚክ ፊት ለፊት የተገነባው 20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል መርቀን ከፍተናል ብለዋል።

የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከልን ወደ ሥራ ለማስገባት ስናቅድ ከሆቴሎች ምግብ እንዲመጣ ነበር። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን ተባባሪነት በምገባ ማዕከሉ ምግብ ማዘጋጀት እንደተቻለ ገልፀው፤ ምድራችን እንዲባረክ አረጋውያንን እና የተቸገሩትን መርዳት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በማዕከሉ ምርቃት ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለአካባቢው አቅመ ደካሞች ማዕድ አጋርተዋል፡፡

20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል የተገነባው በቶኩማ ቢዝነስ ግሩፕ ሲሆን በቋሚነት ምገባ የሚያከናውነው ደግሞ ብዟየሁ ፋውንዴሽን ነው። ማዕከሉ አምሥት መቶ አረጋውያንን እና አቅመ ደካሞችን በቀን አንድ ጊዜ የሚመግብ ሲሆን ለአሥራ ስድስት እናቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።

# ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ሰባት ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ አቅዷል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት በአገልግሎት እና በማምረቻ ዘርፍ ሰባት ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ ማቀዱን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ዕቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ እናትነሽ ታመነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ በዋናነት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው በመጀመሪያ ደረጃ የአገልግሎት ዘርፍ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በ2016 በጀት ዓመት ኮሚሽኑ ከአገልግሎትና ከማምረቻ ዘርፍ ሰባት ቢሊዮን ብር ለማስመዝገብ ያቀደ ሲሆን ከኢንቨስትመንት ፍቃድ እና ከተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶች 26 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

እንደ ወይዘሮ እናትነሽ ገለጻ፤ በዚህ ዓመት ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ለ700 ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡ ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች አብዛኛው በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሚሰጡ በመሆኑ በተያዘው በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ኦንላይን ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡ የኮሚሽኑን የመረጃ አያያዝ ሥርዓትም ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራ በዚሁ በጀት ዓመት ለመሥራት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

ባለሀብቶች የሚጠይቁትን የድጋፍ አገልግሎቶች ፈጣን እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለማስተናገድ እና በተደጋጋሚ የሚያነሷቸውን የመሬት እና የብድር ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ አመራሩ በትክክል መሥሪያ ቦታው ላይ በመሄድ ችግሩን የማጣራት ሥራ እየሠራ ይገኛል ያሉት ወይዘሮ እናትነሽ፤ ተቋሙ እነዚህን የባለሀብቶች ጥያቄ በዘላቂነት ለመፍታት እንዲያመች ከተቋማት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ሰነዶች አዘጋጅቶ በመፈራረም ላይ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ኮሚሽኑ የገቢም ሆነ የአገልግሎት ዕቅዱን ለማሳካት በዋናነት ለባለሀብቱ ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፤ ባለሀብቱ ባለበት ሆኖ ስለ ኢንቨስትመንት መረጃ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ የኦንላይን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ እንዲሁም ለአገልግሎት ክፍያዎችን በካሽ እና ከፖስ ማሽን በተጨማሪ በቴሌብር እና በሲቢኢ ብር እንዲጠቀሙ ማድረግ የዚህ ዓመት ሁነኛ ሥራዎች ናቸው ሲሉም ገልጸዋል ዳይሬክተሯ፡፡

# የሽናሻ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ «ጋሪ ዎሮ» በዓል በአሶሳ ከተማ ተከበረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚከበሩት ዓመታዊ በዓላት መካከል የሽናሻ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ «ጋሪ ዎሮ» በዓል በአሶሳ ከተማ ተከበረ።

በዓሉ በየዓመቱ መስከረም ወር አጋማሽ ላይ የሚከበር ሲሆን በዓሉን ለመታደም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች ይሰባሰባሉ። በዓሉ ትናንት በአሶሳ መከበር የጀመረው በብሔረሰቡ ታላላቅ አባቶች ባደረጉት የምርቃ ሥነ-ሥርዓት ነው።

የብሔረሰቡ የሀገር ሽማግሌ አቶ ለማ አልጋ ለኢዜአ እንደገለፁት፣ በዓሉ የብሔረሰቡ አባላት ወደ አዲስ ዓመት በመሸጋገራቸው ለፈጣሪያቸው ምስጋና የሚያቀርቡበት ነው።

የበዓሉ አከባበር በሀገር ሽማግሌዎች ምርቃት የሚጀመር ሲሆን በእዚህም አዲስ የለማ ሰብል በረከት እንዲኖረው ከመመኘት በተጨማሪ ዓመቱ እንደሀገር ሰላምና ደህንነት የሰፈነበት እንዲሆን ያለመ መሆኑን አስረድተዋል።

በእዚህም የሀገር ሽማግሌዎቹ ለአዲሱ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ፤ ዘመኑ የሰላምና የፍቅር ይሁንላችሁ እያሉ ይመርቃሉ ብለዋል። በበዓሉ መክፈቻ ላይ ከምርቃት



ጎንለጎን ደመራ የመለኮስ ሥነ-ሥርዓት ተካሂዷል።

አቶ ለማ እንዳሉት በዓሉ ከመከበሩ አስቀድሞ በሽናሻ ብሔረሰቡ ባህል መሠረት የተጣሉ እንዲታረቁ እና ፍቅር እንዲያወርዱ ይደረጋል። በእዚህም በብሔረሰቡ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የጋሪ ዎሮ በዓል የእርቅና የአንድነት በዓል በመባልም እንደሚታወቅ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ለማ ገለጻ፤ የሽናሻ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ «ጋሪ ዎሮ» በዓል ሲከበር የተቸገሩ ሰዎችን ከመርዳት በተጨማሪ በዓሉን በአብሮነት ማሳለፍ የባህሉ እሴቶች ናቸው።

በበዓሉ የብሔረሰቡን ባህላዊ እሴቶች በመጠበቅና በማጎልበት ለትውልድ ማስተላለፍ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የብሔረሰቡ ምሁራን እና ተወላጆች ያካተተ የፓናል ውይይት እንደሚደረግም ታውቋል።

የጋሪ ዎሮ የዘመን መለወጫ በዓል በአሶሳ ከተማ ሲከበር ዘንድሮ ለ13ኛ ጊዜ ሲሆን የሽናሻ ብሔረሰብ አባላት በስፋት በሚገኙበት ገጠራማ አካባቢም ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ በታላቅ ድምቀት እንደሚከበር ታውቋል።

# ከክልሉ የማዕድን ወጪ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሌላኛው ሰፊ የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንደሚያስገኝ የሚጠበቀው የማዕድን ምርት ኦፓል ነው ያሉት አቶ ታምራት፤ ማዕድኑ በስፋት በሰሜን ሸዋ፣ በሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ከማዕድን ወጪ ንግድ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ መታቀዱን አቶ ታምራት አመላክተዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ የማዕድን ገቢ 75 ሚሊዮን ብር መገኘቱን ያነሱት ምክትል ኃላፊው፤ በ2016 በጀት ዓመት ገቢውን ወደ 100 ሚሊዮን ብር ለማሳደግ መታቀዱን አስታውቀዋል።

አቶ ታምራት እንደገለጹት፤ የተቀመጠውን እቅድ ለማሳካት በክልሉ የሚገኙ ማዕድናት ያሉበትን ቦታ፣ የክምችት መጠናቸውንና ዓይነታቸውን የመለየት ሥራዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።

ከጥናትና የቦታ መረጣ ሥራዎች በተጓዳኝነት የማዕድን ክምችታቸው በተረጋገጡ ቦታዎች ላይ ባለሀብቶች ገብተው እንዲሠሩ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በሚከናወኑ የማዕድን ልማትና ንግድ ሥራዎች ለ45 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ መያዙን አመላክተዋል፡፡

በተለይ ወጣቶች በማዕድን ቁፋሮና እሴትን ጨምሮ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበት ሰፊ ዕድል እንዳለ አቶ ታምራት ጠቁመዋል።

ከሥራ ዕድል ፈጠራው ባለፈ ሕጋዊ ነጋዴዎችና የማዕድን አውጪዎች ላይ ጉዳት እያደረሰ የሚገኘውን ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን ለመከላከል የተቋቋመውን ግብረኃይል ድጋሚ በማዋቀር ሥልጠናና አስፈላጊውን ግንዛቤ



**አቶ ታምራት ደምሴ**

የማስጨበጥ ሥራ እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

ከቁጥጥር ሥራው ባለፈ ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርና ንግድን ለመከላከል የወጣው መመሪያ 10 ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑም ተሻሽሎ ሥራ ላይ እንዲውል የሚረዳ ዝግጅት እየተከናወነ መሆኑን አስረድተዋል።

ሕገወጥ የማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚረዳ የሕግ ማዕቀፍ ለክልል ምክር ቤቱ ቀርቧል ያሉት አቶ ታምራት፤ ከፍትህ ቢሮ አስተያየት እንደተሰጠበት አመላክተዋል።

በቀጣይም ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍና ቁጥጥርን ተግባራዊ በማድረግ የማዕድን ዘርፉ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

# በሰሜን ጎንደር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አጋማሽ ጀምሮ በተከሰተው ድርቅ 452 ሺህ ዜጎች ተጎድተዋል፡፡ በተለይ 202 ሺህ ዜጎች አስቸኳይ የምግብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንደ አቶ ሰላምይሁን ገለጻ፤ በዞኑ በሚገኙ ጃናሞራ፣ ጠለምት፣ የበየዳ ወረዳዎችን ጨምሮ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ጠለምትና የተወሰኑ የደባርቅ አካባቢዎች በድርቅ ተጎድተዋል፡፡

ከግንቦት አጋማሽ ጀምሮ ዝናብ በወቅቱ ባለመዝነቡ ሳቢያ በዞኑ በሚገኙ ስድስት ወረዳዎች ለድርቅ ተጋልጠዋል ያሉት አቶ ሰላምይሁን፤ በድርቁ ሳቢያ 19 ሺህ አምስት መቶ ሄክታር ሰብል ጉዳት እንደደረሰበት አመላክተዋል፡፡ በዞኑ በሚገኙ ወረዳዎች በተከሰተው የዝናብ እጥረት 103 ሺህ እንስሳት ለድርቅ አደጋ መጋለጣቸውን ጠቁመው፤ 53 ሺህ የሚደርሱ እንስሳት በድርቁ ሳቢያ መሞታቸውን ተናግረዋል፡፡

በጠለምትና ጃናሞራ ወረዳዎች በድርቁ ምክንያት ከአራት ሺህ በላይ ዜጎች ከአካባቢያቸው ለቀው ወደ ወረዳ ማዕከላት መምጣታቸውን በመግለጽ፤ ዞኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ለማቅረብ ጥረት በማድረግ ላይ ነው ብለዋል፡፡

የድርቅ አደጋ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ክልሉ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ኩንታል በላይ የምግብ ድጋፍ ማድረጉን የገለጹት አቶ ሰላምይሁን፤ ድጋፉን የችግሩ ተጋላጭ ለሆኑ 14 ሺህ ዜጎች ማድረስ ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በድርቁ አካባቢዎች ላይ ተላላፊ በሽታዎች በተለይም የኮሌራ በሽታ መከሰታቸውን አስታውቀው፤ የዞንና የክልሉ ጤና ቢሮዎች ችግሩን ለመፍታት ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ላይ ለሚገኙ ዜጎች አስቸኳይ የዕለት ምግብ፣ መድኃኒቶች፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጨምሮ ውሃና የእንስሳት መኖ ድጋፍ አስፈላጊ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ዞኑ የተለያዩ ግብረ ኃይሎችን በማቋቋም ሀብት የማፈላለግ ሥራ ጀምሯል ያሉት ኃላፊው፤ የችግሩ ሁኔታ ከቀን ወደቀን እየከፋ በመሄዱ የሚመለከታቸው አካላት የጀመሩትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በድርቁ ሳቢያ ዜጎች ለከፋ ችግር እየተጋለጡ በመሆኑ ሁሉም አካላት ሊረባረቡ እንደሚገባ በመግለጽ መንግሥት፣ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ አጋር አካላት የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያቀርቡ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# የበጎ ፈቃድና በጎ ምግባር አዝመራዎች

**በኃይሉ አበራ**



አቶ አብርሃም ታደሰ



አቶ ዘላለም ብርሃኑ



ወጣት ሰላማዊት ነዒም

በሀገራችን መረዳዳት እና መደጋገፍ የቆየ እሴት መሆኑ ይታወቃል። ቀድሞውንም የነበረ ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት ያለው ከመሆኑም ባሻገር ባህላዊ እሴት መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል። በርካታ ዜጎች በእነዚህ ምሳሌዎች ለብሰዋል፤ ጎርሰዋል፡፡ መኖሪያ ቤታቸው ቀና ተደርጓል፤ አመት በዓል ሲደርስ ቤታቸው አመት በዓል አመት በዓል እንዲሸት ሆኗል፣ ወዘተ.፡፡

በሀገራችን አሁንም በርካታ የመንግሥትንና የማኅበረሰቡን ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎች ይገኛሉ። በተቋም ደረጃ ሊሠሩ የሚያዳግቱ ኀብረትን፣ በጎ ፍቃደኝነትን የሚጠይቁ አያሌ ማኅበራዊ ኃላፊነቶችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ዜጎች በመታደግና ማኅበራዊ ኃላፊነቶች በመወጣት በኩል በአንዳንድ ተቋማት የሚከናወኑ ተግባሮች እንዳሉ ሆነው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ኅብረተሰቡን እያስተባበረ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እየሠራ ይገኛል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ዜጎችን ለመታደግ በተነሳሽነት እያከናወናቸው ያሉ የመደጋገፍ ምግባሮች ጎልተው እየታዩ ነው፡፡ በመንግሥት አነሳሽነት እየተከናወኑ ያሉ የመደጋገፍ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች በማኅበረሰቡ ብሎም በሀገር ደረጃ እየጎለበተ እንዲመጣ እያደረገም ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በበዓላት ወቅት አቅሙ የፈቀደ ሰው እጁ ያጠረበትና ድጋፍ የሚሻ ወገኑን «አለሁ ባይነትን» ማሳየቱ፣ ማዕድ ማጋራቱ እየጎለበተ መጥቷል፤ መኖሪያ ቤታቸው ለፈረሰባቸው መኖሪያ ቤት መጠገን እየተለመደና ባህል እየሆነ ይገኛል፡፡ በደም ልገሳ፣ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር፣ በትራፊክ ማስተናበር እየተሠሩ ያሉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች እየሰፉና እየተለመዱ መጥተዋል፡፡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡

ወይዘሮ መስከረም አብርሃ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ የቤት እድሳት እድል ተጠቃሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የቀድሞ መኖሪያ ቤታቸው ለኑሮ ምቹ አልነበረም። ፈሳሽ ውሃ የሚያልፍበት ቱቦ የነበረበት እንዲሁም በቆርቆሮ የተሠራ ለቅዝቃዜ የሚያጋልጥ ነበር። በዚህ ቤት ውስጥ ከአምስት ልጆቻቸው ጋር ለመኖር ተገደው እንደነበር ወይዘሮ መስከረም ያስታውሳሉ።

«አሁን በተሻለ ቤት ውስጥና የኑሮ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን» የሚሉት ወይዘሮ መስከረም፤ አቅመደካሞችን በመለየት ለቤት እድሳት ተጠቃሚ መደረጉም በማስመልከት የከተማ አስተዳደሩ፣ የወረዳ እና የብሎክ አመራሮች ጨምሮ ሁሉም ድጋፍ ያደረጉ ተቋማት እና ባለሀብቶችን አመስግነዋል። አቅመ ደካማ የሆነን ሰው መንገድ ከማሻገር ጀምሮ መደጋገፍ ያለው ለሌለው ማሰቡ ደስታን የሚሰጥ በመሆኑ እርሳቸውም በተመሳሳይ አቅም በፈቀደ ሁሉ ለተቸገሩት መልካምነትን በማድረግ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ለመጋራት እንደሚያስቡም ተናግረዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳው አንድ በጎ ፈቃድ ቡድን አስተባባሪ ወይዘሮ አመለ አለባቸው በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በ90 ቀናቱ በተደረገ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሠሩ ሥራዎች በገንዘብ ቢተመኑ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ የሚደርስ ነው። በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መመገብ የማይችሉ 179 ሰዎች ከሆቴሎች ጋር የማስተሳሰር ሥራ ተከናወኗል። 116 ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል። 377 ሰዎችም በከተማ ግብርና ተጠቃሚ ተደርገዋል። 30 ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ ተነስቷል። ማዕድ በማጋራትም በመጀመሪያ ዙር 636፣ በሁለተኛ ዙር 695 ሰዎች የተጠቀሙ መሆኑን ተናግረው እንዲሁም ለመስቀል በዓል 118 ሰዎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አስተባባሪዋ ይገልፃሉ።

«ስድስት አባወራዎች የቤት እድሳት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል» የሚሉት አስተባባሪዋ፤ በአንደኛ ዙር ከሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሁም በሁለተኛ ዙርም ከአንድ ነጥብ 69 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሥራ መሠራቱን ይናገራሉ።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘላለም ብርሃኑ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በበዓሉ ዋዜማና ከበዓሉ ማግስትም ከተማዋን ፅዱና ውብ በማድረግ በተለይ በመስከረም ወር የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት ዜጎች በነፃነት እንዲያከብሩ የመሥራት ሥራዎች ተከናውነዋል።

በዓሉ ያለው ለሌለው እያካፈለ በመተሳሰብ፣ በአብሮነት እና በመደጋገፍ ማክበር ይገባል የሚሉት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ ከበዓሉ ጋር ተያይዞ ከተማዋን የሚያቆሽሹ ጉዳዮች ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ በበዓሉ ማግስትም በቀጣይነት ማጽዳት እንደሚገባ በዚህም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በወጣቱ መሰጠት እንደሚኖርበት ገልፀዋል።

የመስቀል፣ የእሬቻ በዓልን ጨምሮ በርካታ በዓላት መከበሪያ እና የቱሪዝም ወቅት በመሆኑ ከተማዋ እንደከዚህ በፊቱ በቆሻሻ እንዳትታወቅ ሁሉም አካባቢውን አጽድቶ ከተማዋ ጽዱና ውብ ለቱሪስት እንድትሆን ለማድረግ የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እየተሠራ መሆኑንም። ከከተማ ውበት እና ፅዳት ጋር ተያይዞም ከተማዋን ከማስዋብ ጀምሮ ከብሎክ እስከ ክፍለከተማ ያለው ሁሉም አካባቢውን ለማስዋብ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በክፍለ ከተማው በበጎ ሥራዎች ጋር ተያይዞ ክረምቱን በሙሉ ቤት የፈረሰባቸውና ቤት የሌላቸውን የማገዝ ሥራዎች መሠራቱን ገልፀዋል። ባለፉት ስድስቱ የጳጉሜ ቀናት ብቻ ከ35 ሺህ በላይ ለሆኑ ሰዎች ማዕድ የማጋራት ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል። በክፍለ ከተማ በሚደረጉ የጽዳት ንቅናቄዎችም በየወረዳው ስድስቱን የጳጉሜ ቀናት የፅዳት ንቅናቄ ወቅት ኅብረተሰቡ ወጥቶ አካባቢውን የሚያጸዳበት ከተማዋን የሚያጸዳበት የቆሸሹ የውሃ ማስተላለፊያ ቦዮችን የሚያጸዱበት ሁኔታዎች ነበሩ፤ በቀጣይነትም ይሠራል ብለዋል።

በክረምት የበጎ ፈቃድ ፕሮግራሞች ውስጥ አንዱ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመከላከል ነው። በዚህም በበጎ ፈቃደኝነት ትራፊክ ፖሊስን በማገዝ እግረኛ መንገድ እንዲያቋረጡ የሚያግዙ አስተናባሪዎች ይሳተፋሉ።

ወጣት ሰላማዊት ነዒም በበጎ ፈቃደኝነት ትራፊክ በማስተናበር ትሠራለች። የዝግጅት ክፍላችን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ለገሐር አካባቢ ስታስተናብር አግኝቷታል። በጎ ፈቃደኛ ለ8 ወራት መሥራቷን ትናገራለች። ሰዎች ብዙ ጊዜ በሃሳብ ላይ ሆነው መንገድ ሲያቋርጡ ለአደጋ ስለሚጋለጡ ሕይወት ለመታደግ በፈቃደኝነት እየሠራች ትገኛለች። ኅብረተሰቡ መንገድ ሲያቋርጥ መጠንቀቅ እንደሚገባው በማስገንዘብ በፈቃደኝነት ለሚደረገው ትራፊኩን የማስተባበር ሥራም እገዛ እንዲያደርጉና በታዛዥነት በእግረኛ ማቋረጫ ብቻ እንዲሻገሩ ትመክራለች።

«እግረኞች ለተሽከርካሪ አደጋ እንዳይጋለጡ እና አካል ጉዳተኛ እንዳይሆኑ በምሰጠው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በጣም ደስተኛ ነኝ» የምትለው ወጣቷ ባለፉት ስምንት ወራት ጠዋት 12 ተኩል እስከ አራት ሰዓት፤ ከሰዓት ከዘጠኝ ተኩል እስከ 12 ሰዓት ተኩል ኅብረተሰቡን እያገለገለች እንደሆነ ትናግራለች። ኅብረተሰቡ በተለይ በበዓላት ቀናት እና የአደባባይ በዓላት በሚከበርበት ወቅት እራሱን እና ቤተሰቡን ከተሽከርካሪ አደጋ እንዲጠብቅ አሳሰባለች።

የመደጋገፍና በጎ ምግባርን እንደ ባህል የማስረፅ የቆዩ እሴቶችን ተቋማዊ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በመንግሥት ስር ተቋቁመው በተደራጀ መልኩ በጎ ምግባር ሥራን ከሚሠሩት ተቋሞች ውስጥ የኅብረተሰብ ተሳትፎ እና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አንዱ ነው። በተለይ በመዲናዋ በተለያዩ በጎ ፈቃድ አገልግሎት እና ፕሮግራሞች በማስተባበር ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎ እና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽነር አቶ አብርሃም ታደሰ እንደሚገልፁት፤ በ2015 በጀት ዓመት በ14 ፕሮግራሞች እና 18 መርሃ ግብሮች መጀመሩን ያስረዳሉ። ከስድስት ሺህ 415 በላይ ቤቶች ታድሰው ለኅብረተሰቡ የተላለፉ ሲሆን፤ በማዕድ ማጋራትም ከ800 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። በልዩ ፍላጎቶች ላይም ትምህርትና ሥልጠናዎች በማጠናከሪያ ትምህርት፣ በቀይ መስቀል ደም ልገሳ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት፣ የአካባቢ ሰላም፣ የኪነጥበብ እና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችና የወሰን የለሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጭምር ተሰጥተዋል።

ኮሚሽነሩ የወሰን የለሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በሲዳማ ክልል በኦሮሚያ፣ በድሬዳዋ፣ እና በተለያዩ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ልምድን የማካፈል እና የበጎ ሥራዎች በጋራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። በአጠቃላይ በበጎ ፈቃድ ሥራዎች ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የሚገመት ሀብት ሥራ ላይ የዋለበት እና ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የከተማዋ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሆኑበት መሆኑን አንስተዋል። ትግበራዎቹም ማኅበረሰቡ ከተጋገዘ እና ከተረዳዳ የማይሻገረው ችግር እንደሌለ ማሳያ መሆኑን ያስረዳሉ።

«የክረምቱ ወር በጎ ፈቃድ አገልግሎት ግንቦት ወር የተጀመረ ሲሆን ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ በጎ ፈቃደኞችን በማሳተፍ የተጀመረ ነው» የሚሉት ኮሚሽነሩ፤ በዚህም ሦስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የሚገመት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት እንደታሰበ ይገልፃሉ። መርሀ ግብሩም እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ መሆኑንም ይናገራሉ። በክረምቱ በአጠቃላይ ከተጀመሩት ሦስት ሺህ ሁለት መቶ በላይ የቤቶች እድሳት አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ በነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተጠናቀቁ አንድ ሺህ 686 ቤቶች መተላለፋቸውን ተናግረዋል። ቀሪዎቹም በቀጣይ ጊዜ እየተጠናቀቁ ለነዋሪዎች እንደሚተላለፉም አመላክተዋል።

አቶ አብርሃም እንደሚናገሩት፤ በተለይ የቤት እድሳት መርሃ ግብሩ ሰፊ ካፒታል የሚጠይቅ በመሆኑ ስድስት ሺህ 415 ቤቶች ተገንብተው ከተሰጡት መካከል ከአንድ ሺህ 30 በላይ የሚሆኑት ቤቶች በሕንፃ ደረጃ ተሠርተው የተሰጡ መሆናቸውን ይናገራሉ። እነዚህም ቤቶች በዝቅተኛ ደረጃ ውስጥ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ለሀገር ባለውለታዎች ሆነው ለችግር የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ የሚያደርግ ነው። ግንባታውን ለማከናወን የከተማዋ ባለሀብቶች ሚና ከፍ ያለ መሆኑ በመግለፅም በተመሳሳይ እቅዱን እውን ለማድረግ ወጣት በጎ ፈቃደኞች ተቋማት ሰፊ ርብርብ እያደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

«በኑሮ ውድነት ምክንያት ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ በተሠራ ሥራም በ2015 በጀት ዓመት ከ800 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል» የሚሉት ኮሚሽነሩ፤ በክረምቱ እና በበዓሉም ከ300 ሺህ በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል። የበጎ ሥራ ትግበራው በዝቅተኛ ኑሮ የሚገኙ ነዋሪዎችን ከማገዙ በተጨማሪ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍሉን በማረጋገጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን በመፍጠር፣ ማኅበራዊ ችግርን በመፍታት፣ በተዘዋዋሪም የተረጋጋ ፖለቲካ ሁኔታን በመፍጠር ረገድ የጎላ ሚና እየተጫወተ እንደሆነም አስረድተዋል።

አቶ አብርሃም በጎ ፈቃደኝነት እርዳታ ሳይሆን ከልብ ወገንን መደገፍና ቸር መሆንን እንደሚጠይቅ ገልፀው፤ ወገንን የማገዝ፣ የመረዳዳት እና የመደጋገፍ ጉዳይ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ይናገራሉ። አሁን በጎ የሚደረግላቸው ሰዎች ነገ ለሌሎች የሚደርሱ በመሆኑም ተዘዋዋሪ እና ተሻጋሪ ውጤት ያለው መሆኑንም ይገልፃሉ። አያይዘውም አንድ ሰው ታሞ መንገድ ላይ ቢወድቅ ድጋፍ የሚያገኘው ገንዘብ ስላለው ወይም ሀብት ስላለው ሳይሆን በተገቢው ቦታና ጊዜ የሚደግፈው ሰው ሲገኝ መሆኑን አንስተው፤ የማኅበረሰቡ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ ይገልፃሉ። እንዲሁም በጎነት ከፍተኛ የኅሊና እርካታ የሚገኝበት እንደማኅበረሰብ ደግሞ ለሌሎች ደስታን እየፈጠሩ ለራስ የኅሊና ሰላም ለመገብየት ትልቅ አቅም በመሆኑ ሊሰፋ እና ሊያድግ የሚገባ መሆኑን አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ወጣቶች በኢሬቻ በዓል

እፀገነት አክሲሱ

‹‹ወጣት የነብር ጣት›› የሚለው አባባል በምክንያት ነው፡፡ በጉልበትም፣በአዕምሮም ያለውን አቅም ለማሳየት ነው፡፡ ወጣትነት ሮጦ ማሸነፊያ ዕድሜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙ ነገሮች ይጠበቃል። ተምሮ እራስን በኑሮ ለመቀየር፣ሀገርምን ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር የወጣትነት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ይመከራል፡፡

‹‹ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አየወጣም›› እንደሚባለው የወጣትነት ዕድሜን ጉልበት ማሳያ አድርጎ ለመጠቀም መሞከር የኋላ ኋላ የሚያስከትለውን ጉዳት ከወዲሁ ግንዛቤ መያዝም ሌላው ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ወጣትነት ላይ የተሠራ ጠንካራ መሠረት ለውጤት ያበቃል፡፡ በተበላሸ መስመር የተጓዘ ደግሞ ቀጣይ ኑሮውም የተበላሸ ይሆናል። ለዚህም ነው ወጣቶች የነገ መሠረታቸው እንዳይበላሽ ታላላቆች፣ምሁራን አበክረው ምክር የሚሰጡት፡፡

ወጣቶች ለነገሮች ችኩል በመሆናቸው፣ ዛሬ ሀገር ለማተራመስና ለእኩይ ተግባር ተኝተው የማያድሩ አንዳንዶች ወጣቶችን ለእኩይ ተግባራቸው ማስፈጸሚያ ሲጠቀሙባቸው ይስተዋላል፡፡ አስተዋይ የሆኑ ወጣቶች ግን ለራሳቸውም ለሀገርም በሚጠቅም ተግባር ላይ ተሰማርተው ሌላውንም ያድናሉ፡፡የሚፈለገውም እንዲህ ያለ ወጣት ነው፡፡

ወጣትነታቸውን በአግባቡ ተጠቅመው፤ የተማሩ፣ የሠሩ፣ ጥሪት የያዙ፣ ቤተሰብ የመሠረቱ ለሀገራቸው በሚችሉት ሁሉ አስተዋጽኦን ያበረከቱ ኋላ ማምሻ ዕድሜያቸው ላይ የዘሩትን የሚያጭዱ፣ አዝመራቸውን በጥሩ ሁኔታ የሚሰበስቡ ይሆናሉ፡፡ እንዲህ ያሉ የሀገር ባለውለታዎች ክብርና ሞገስ ያገኛሉ፡፡ ይዘከራሉ።ለተተኪ ትውልድም በአርአያነት ይጠቀሳሉ፡፡ ተሞክሮአቸውም ለተተኪው ትምህርት ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ስማቸው ከፍ ብሎ የሚነሳ በተለያየ መንገድ ባለውለታዎችን አፍርታለች፡፡ ወጣትነት ይህ ሁሉ በረከቶች የሚገኝበት እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ብዛት ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው ወጣት ኃይል ነው፡፡ ይህ ኃይል በማኅበራዊ እሴት፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካው ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ይጠበቃል፡፡ መንግሥት ይህ ኃይል በተለያየ አደረጃጀት ሆኖ እራሱንና ሀገሩን እንዲጠቅም የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱም አይዘነጋም፡፡ሆኖም ግን የሚፈለገውን ፍሬያማ ውጤት በማምጣት ደረጃ ብዙ ሥራ ይጠበቃል፡፡

ወጣቶች የልማትና የሰላም ሞተር የሆኑትን ያህል በትንሽ ነገር ስሜታዊ የሚሆኑበት አጋጣሚዎች የበዙ ናቸው፡፡ ጠያቂዎችም ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ላቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ታጋሽ አይደሉም፡፡ በዚህም ስህተት ውስጥ ሲገቡ ይስተዋላል፡፡ ነገሮችን ከማመዛዘን ቁጣና ፀብን አማራጭ ያደርጋሉ፡፡እኩይ ተግባር ያላቸው አንዳንድ አካላትም እነዚህን ድክመቶቻቸውን በመጠቀም ለጥፋት መሥሪያቸው ያደርጓቸዋል፡፡

ወጣቶች በዕድሜያቸው ሊያገኟቸው የሚፈልጓቸውን ነገሮች ማሟላት የቻሉ እንደሚጠቀሙ መዘንጋት የለበትም፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግን የሀገር አቅምና ከፍተኛ ቁጥር ካለው የወጣት ኃይል ጋር የተጣጣመ ነገር ለማድረግ አዳጋች ነው፡፡ ወጣቱ የሚፈልገውን የትምህርት ዓይነትና የሥራ ዕድል ተደራሽ ማድረግ በአቅም የሚወሰን በመሆኑ የተሟላ ምላሽ ላይገኝ ይችላል። በዚህም በወጣቱ ሁለተናዊ ተጠቃሚነት ላይ ክፍተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

ወጣቱ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሀገሩን ለጥቃት አሳልፎ የሚሰጥ እንዳልሆነ በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የተነሱ ኃይሎች እንዳይሳካላቸው በመታገል በተግባር አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያ በሚጠራበት ሁሉ ‹ሆ› ብሎ የሚነሳ ወጣት ያላት መሆኗ ምስክር መጥራት አያሻም፡፡

እንዲህ ያለውን መልካም ወጣት ጭምር ለእኩይ ተግባራቸው ለመጠቀም የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በተለይም ቀደም ብለን ባሳለፍነው የጥምቀት፣ አሁን ደግሞ ከፊታችን ለምናከብረው እሬቻና ሌሎችም የዓደባባይ በዓላትን ለመረበሽ መሠረት አድርገው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

በነዚህ ወቅቶች ወጣቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ከአጓጉል ነገሮች እራሳቸውን በመጠበቅ፣ ለእኩይ ተግባራቸው መሣሪያ ሊያደርጓቸው የሚፈልጉ



አካላትንም ፊት ነስተው፣ ለሀገራቸው ሰላም ዘብ መቆም ያለባቸው ጊዜ አሁን ነው። ለሀገራቸው ሰላም ዘብ መቆም መቻላቸው ደግሞ ለነገ እነሱነታቸው ብሎም በሀገራቸው ተከብረውና በአቅማቸው ሠርተው ከበሬታንም አትርፈው ለመኖር እርሾው የሚሠራው ዛሬ መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ የሚከበረውን የኢሬቻ በዓል ባህላዊና ሃይማኖታዊ እንደምታውን ባልለቀቀ፣ ከእኛ እልፎ ለሌሎች ደስታን በሚፈጥር መልኩ ይከበር ዘንድ የወጣቶች ሰላም ወዳድነት አብሮ ተቀናጅቶ ለሰላም መሥራት ከምን ጊዜውም በላይ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም፡፡

በዋናነት ግን በኢትዮጵያ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፤ በቢሾፍቱ ከተማ ደግሞ የሆራ ሃር-ሰዲ መስከረም 25 እና 26 ቅዳሜ እና እሁድ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በታደመበት በዓሉ ይከበራል። የኢሬቻ በዓል ላይ በሰላምና በፍቅር ለመታደም በመጠባበቅ ላይ ያሉትን ወጣቶች አነጋግረናል። ከዚያ በፊት ግን በዓሉን በተመለከተ ትንሽ ነገር እንበል።

### ኢሬቻ ምንድን ነው?

ኢሬቻ የምስጋና በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የኢሬቻ በዓልን ያከብራል ይላሉ የማኅበረሰቡ ባህላዊ መሪዎች። የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል ነው ኢሬቻ።

የኦሮሞ ታሪክ ምሁራን እንደሚሉት፤ «ኢሬቻ ማለት ዋቃ (ፈጣሪ) የፈጠረውን ማመስገን ማለት ነው»። በዓሉም ማኅበራዊ ደረጃ እና የዕድሜ ልዩነት ሳይፈጠር የኦሮሞ ሕዝብ የኢሬቻ በዓልን ለዘመናት በጋራ ሲያከብር ቆይቷል። ኢሬቻ የዘመን መለወጫ በዓልም ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱ በማለፉ በኢሬቻ ቀን ምስጋናውን ለፈጣሪ ያቀርባል።

በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ መስከረም ላይ ይገናኛል። ሕዝቡም ክረምቱን በፈጣሪ ፍቃድ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከዘመድ አዝማድ አገናኘን ብሎ ምስጋና ያቀርባል። ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና ያቀርባል።

«ክረምት ሌሊት ነው። ሌሊት ደግሞ ጨለማ ነው። ጨለማ ለአውሬ እንጂ ለሰው ልጅ አይሆንም። ጨለማው ሲነጋ ደግሞ ብርሃን ነው፤ ብርሃን ሲሆን ሃሳብ የለም ደስታ ይሆናል። 'መስከረም በረ'ባ ማለት ይህ ነው» በማለት የኦሮሞ ሕዝብ ከክረምት መገባደድ በኋላ የኢሬቻ በዓልን የሚያከብርበትን ምክንያት እነዚሁ ምሁራን ያስረዳሉ።

የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚወጣ ታዳሚ እንደ ሳር ወይም አበባ ያለ እርጥብ ነገር በእጁ ይዞ መገኘቱም አንዱ መገለጫው ነው። «'ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው፤ ለዚህም እናመስግንሃለን' በማለት እርጥብ ነገር ተይዞ ይወጣል» ሲሉ የታሪክ ምሁሩ ይናገራሉ።

### ኢሬቻ ለሠላም እና እርቅ

በኢሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ለመላው የሰው ልጅ ሠላምና ደኅንነት ፈጣሪውን ዋቃን ይለምናል፤ ያመሰግናል። «የተጣላ ታርቆ፣ ቂሙን ትቶ በነፃ ልቦና ፈጣሪ ንጹህ ወዳደረገው የውሃ አካል ይሄዳል። ኢሬቻ ቀልብ የሚነጻበት ቦታ ነው» ስለመሆኑ ይገልጻሉ።

### መልካ እና ቱሉ

የኢሬቻ በዓል ሁለት ጊዜ ይከበራል። እነዚህም የክረምት ወራት እንዳበቃ የሚከበረው ኢሬቻ መልካ (የውሃ አካል ዳርቻ የሚከበር) እና በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚከበረው ኢሬቻ ቱሉ (በተራራማ ቦታ) የሚከበሩ ናቸው።

የታሪክ ምሁራኑ ኢሬቻ መልካ የምስጋና በዓል ሲሆን ኢሬቻ ቱሉ ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን የሚለምንበት በዓል ነው ይላሉ። «በበጋው የፀሐይ ሃሩር ሰው እና ከብት በሚቃጠልበት ጊዜ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብ የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ተራራ ወጥቶ ፈጣሪውን ይለምናል። ተራራ ላይ ተወጥቶ ሲለምን ፈጣሪ ቶሎ ይሰማል የሚል እምነትም አለ» ይላሉ።

«ይህን ተራራ የፈጠርክ ፈጣሪ ወቅቱን የሠላም አድርግልን፣ የሠላም ዝናብ አዝንብልን፣ ጎርፍን ያዝልን፣ የተዘራው ፍሬ እንዲያፈራ እንለምንሃለን» እያለ በኢሬቻ ቱሉ ላይ ፈጣሪውን ይለምናል በማለት ምሁራኑ ያስረዳሉ።

ወጣት ድሪባ ደምሴ በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖር የኦሮሞ ተወላጅ ሲሆን በጉጉት የሚጠብቀው የኢሬቻ በዓልም እየደረሰ በመሆኑ እጅግ መደሰቱን በመግለጽ ከሦስት ዓመት በፊት ሆራ ሀርሰዲ (ቢሾፍቱ) በመሄድ ያከብረው የነበረው በዓል አሁን ላይ በሚኖርበት ከተማ ላይ መከበሩ እጅግ እንዳስደሰተውም ይናገራል።

በዓላት ሁሉ ልዩ ናቸው፡፡ ኢሬቻ የምስጋና፣ የደስታ፣ የሰላም የፍቅር፣ ወር የአብሮነት በዓል ከመሆኑም በላይ የተነፋፈቁ ዘመዳሞች ጓደኞች የሚገናኙበት፣ወጣቶች የሚተጫጩበትና የነገውን ሀገር ገንቢ ቤተሰብ ለመመስረት ቃል የሚያስሩበት ልዩ ቀን ነው። የኦሮሞ ሕዝብም ይህንን በዓል ለዘመናት ተዋዶ በሠላምና በፍቅር ከመላው የኢትዮጵያ ልጆች ጋር ሲያከብር ቆይቷል፡፡ ወደፊትም ያከብራል ይላል።

ወጣት ድሪባ እንደሚለው አሁን ያለንበት ጊዜ እንደ ሀገር ብዙ ችግሮችና መከራዎች ያሉበት ቢሆንም፣ በዓሉን የሰላም እሴቶችን አጠናክሮ ለመቀጠል፣ የተጣላን ለማስታረቅ ሠላምና ፍቅርን የሚያጎለብቱ ሥራዎችንና ሀሳቦችን ለማመንጨትና ለመናገር ጥረት የሚደረግበት እንዲሆንም ፍላጎቱ መሆኑን ያብራራል።

‹‹ሀገራችን ላይ ብዙ ፍላጎቶች አሉ፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ደግሞ እንዲስተናገዱ የሚፈለገው ኢሬቻን በመሳሰሉ የአደባባይ በዓላት ላይ ወጣቶችን በመጠቀም ነው፡፡ ይህ ግን ፍጹም ስህተት የሆነ አካሄድ ከመሆኑም በላይ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ የሚያስከፍለን ነው። እነዚህን የእኩይ ተግባር ነጋዴዎች ለመዋጋትና ሀሳባቸውን ውድቅ ለማድረግ ደግሞ ወጣቶች ትልቅ አቅም አለን›› በማለት ሃሳቡን ሰጥቷል።

ስሜትን ሳይሆን ሀገርን ማስቀደም እንደሚገባና በየአመቱ ተናፍቆ የሚመጣውን የኢሬቻ በዓል የእኩይ ነጋዴዎች መጠቀሚያ እንዳይሆን ወጣቱ ከምን ጊዜውም በላይ የነቃ ሊሆን እንደሚገባም አሳስቧል፡፡

ወጣት አለማየሁ ሙለታ በበኩሉ ኢሬቻ ሁሌም ተናፋቂና በየዓመቱ ሲመጣም ዕድሜና ጾታ ሳይለይ ሁሉንም የሚያስደስት አንድነትና ፍቅር የሚጠነክርበት የሰላምና የምኞት በዓል ነው ይላል።

ወጣት አለማየሁ ‹‹ኢሬቻ ከዘመናት ናፍቆት በኋላ በምንኖርበት መዲና መከበሩ ብዙ ደስታን ፈጥሮልናል፡፡ በዓሉም የምስጋና እንደመሆኑ እኛም ለዚህ ነገር ባገኘነው አጋጣሚ እናመሰግናለን። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በዓሉ የሚጠይቀውን ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴት በሳተ መልኩ ፖለቲካዊ ይዘት ሲሰጠው ይታያል፡፡ ይህ ግን ፍጹም ኢሬቻን የማይገልጽ ከመሆኑም በላይ ሊታረም የሚገባው ነገር ነው›› ሲል ያስረዳል፡፡

‹‹ኢሬቻን ከእኛ በፊት ያሉ እናት አባቶቻችን እህት ወንድሞቻችን በጥሩና ሁኔታ በፍቅርና በሠላም ሲያከብሩት ኖረዋል›› አለማየሁ ምንም እንኳን የአሁኑ ትውልድም የእነሱን ፈለግ በመከተል በዓሉን እያከበረ ቢሆንም የእነሱን ያህል ግን ባህላዊ ሃይማኖታዊ ይዘቱን ጠብቋል ለማለት እንደሚቸገር ይናገራል፡፡ በዓሉ እንደቀደመው ጊዜ በብዙ ፍቅርና መተሳሰብ እንዲከበር ከወጣቶች ብዙ እንደሚጠበቅ ነው ያስረዳው፡፡

እንደ ኢሬቻ ዓይነት የአደባባይ በዓላት በተለይም የሀገርን ሠላምና አንድነት ለማወክ የሚፈልጉ አካላት መጠቀሚያ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው ያለው ወጣት አለማየሁ እነዚህ የችግር ቸርቻሪዎች ደግሞ በዋናነት መጠቀሚያ የሚያደርጉት ወጣቱን ኃይል እንደሆነ በመጥቀስ፣ ወጣቱ ለእኩይ ተግባራቸው ጆሮ ሳይሰጥና ሳያዳምጥ በዓሉ ከምን ጊዜውም በላይ በሠላምና በደስታ በፍቅር እንዲከበር የበኩሉን ማድረግ እንዳለበትም አመልክቷል።

‹‹በዓላት ምን ጊዜም ቢሆን የደስታና የፍቅር የሠላምና የአንድነት ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ የጥፋት ኃይሎች እነዚህን መልካም እሴቶች ለእኩይ ተግባር ስለሚጠቀሙበት ከማንም በላይ ይህንን ሴራ በማክሸፍ የበዓላቱን ሠላማዊነት ሊያስጠብቁ የሚችሉት ደግሞ ወጣቶች ብቻ ናቸውና በዚህ ልክ ወጣቶች ወደራሳቸው በማየት በዓላቱ ሠላማዊ ሆነው እንዲጠናቀቁ የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው›› ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# ሊትየም ወደ ማምረት እየተሸጋገረ ያለው ኩባንያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሃብት ዕምቅ አቅም እንዳላት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ሀገሪቱ ከዚህ እምቅ አቅም እየተጠቀመች ያለችው በተወሰኑት ማዕድናት ለእዚያውም በተወሰነ መጠን መሆኑ ይታወቃል፡፡

ለአብነትም ሀገሪቱ ከወርቅ ማዕድኗ ስትጠቀም የቆየች ብትሆንም አሁንም አብዛኛው አመራረቷ ከባህላዊ መንገድ ያልወጣ ነው፡፡ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ክምችት ቢኖራትም ተጠቃሚ መሆን የጀመረችው በቅርቡ ነው፤ እሱም ቢሆን ከጥራት፣ ከገበያና በስፋት ከማልማት አኳያ ብዙ ሥራዎችን ይጠይቃል፡፡ ሌሎች የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን ግብአት ማዕድናት በስፋት ያላት ቢሆንም በማልማት በኩል ገና ብዙ ይቀራል፡፡

በሌላ በኩልም የማዕድን ሃብቱን ፈልጎ ማግኘት፣ የተገኘውም ማዕድን በምን ያህል ክምችት እንዳለ በማወቅና በማልማት በኩል ገና ብዙ የሚቀሩ የቤት ሥራዎች ይቀራሉ፡፡ ለዚህም ዋናው ማነቆ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩ አንዱ ሲሆን፤ ማዕድንን ለማልማት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በሀገር ውስጥ አለመኖራቸውና ዘርፉ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንደሚጠይቅ የማዕድኑ ዘርፍ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች እየለሙ ያሉት አብዛኞቹ ማዕድናት በመሬት የላይኛው ክፍል የሚገኙና በቀላሉ ሊለሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ በሀገሪቱ በመሬት ውስጥ ያሉ ገና ያልተደረሰባቸው በርካታ ማዕድናት አሉ። እነዚህን ማዕድናት ፈልጎ ለማግኘትና አልምቶ ለመጠቀም ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አልተሠራበትም፡፡

ሀገሪቱ ገና ያልነካቻቸው የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ማዕድናት ባለቤት መሆኗን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሌሎች በቅጡ ያለሙ ማዕድናት እንዳሏትም ይታወቃል።

ሀገሪቱ እምቅ የማዕድን ሀብቶቿን በሚገባ በማልማት ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት ለማዋል በአስር አመቱ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ እቅዷ አካታ እየሠራች ትገኛለች፡፡ ይህን ተከትሎም በከርሰ ምድር ውስጥ ያሉ የተለያዩ ማዕድናትን አውጥቶ መጠቀም የሚያስችሉ ዕድሎች እየተፈጠሩ ናቸው፤ ባለሃብቶችም በስፋት ወደ ዘርፉ እየገቡ ይገኛሉ፡፡

በወርቅ ልማት ዘርፍ ያለውን ብንመለከት በባህላዊ መንገድ ብቻ ሲመረት የኖረውን የወርቅ ማዕድን በኩባንያዎች በስፋት ማምረት የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡ ኩባንያዎቹ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ሲሸጋገሩ በባህላዊ መንገድ ሲመረት የቆየውን ምርት አምስት እጥፍ ማምረት እንደሚያስችሉ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ሰሞኑን ደግሞ የሊቲየም ማዕድንን የሚያለማ ኩባንያ ማሽነሪዎችን ወደ ሀገሪቱ ማስገባት መጀመሩ ተጠቁሟል፡፡ ይህ በዓይነቱ ለየት ያለና የሊቲየም ምርትን ለማምረት ዝግጅቱን ያጠናቀቀው ኩባንያ ቀንጢቻ ማይኒንግ ይባላል። ቀንጢቻ ማይኒንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር፤ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጉጂ ዞን ሰባቦሩ ወረዳ ቀንጢቻ አካባቢ የሚገኝ በማዕድን ዘርፍ የተሰማራ ኩባንያ ነው፡፡ የሊትየም ማዕድንን ለማልማት የተቋቋመው ኩባንያው፣ በውጭ ባለሃብቱ ሚስተር ብሩስ ቲኒ እና በኢትዮጵያዊው ባለሃብት ሼህ ዓሊ ሁሴን ከፍተኛ የሼር ድርሻ የተቋቋመ ነው፡፡

ኩባንያው ለመኪና ባትሪ ምርት ዋነኛ ግብዓት የሆነውን ሊትየም የተባለ ማዕድን ማምረት የሚያስችለውን ፈቃድ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ሊትየምን ፕሮሰስ በማድረግ እሴት ጨምሮ ማምረት የሚያስችለውን የመጀመሪያ ዙር ማሽን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት የሊትየም ምርትን እያመረተ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብበት የመጨረሻው ምዕራፍ


ሚስተር ብሩስ


አቶ ሳሚ ሚሊዮን


ሼህ ዓሊ ሁሴን

ላይ መድረሱን ከሰሞኑ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን ዘመናዊ ማሽኖች ባስጎበኘበት ወቅት ገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ የአፍሪካ ማይኒንግና ኢንጂነሪንግ ተወካይ እና የቀንጢቻ ማይኒንግ ከፍተኛ የሼር ባለድርሻ ሼህ ዓሊ ሁሴን እንዳሉት፤ የሊትየም ማዕድንን አልምቶ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ኩባንያው ባለፉት ሁለት ዓመታት በርካታ ሥራዎችን መሥራቱን ተናግረዋል፡፡ ኩባንያው የሊቲየም ምርትን አግኝቶ በማልማት ቀዳሚ መሆኑን የጠቀሱት ሼህ ዓሊ ሁሴን፤ ኩባንያው በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን ዘመናዊ ማሽን ማስገባቱን አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ማሽኑ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከአውስትራሊያና ከካናዳ በተውጣጡ ኢንጅነሮች የተሠራ ዘመናዊ ማሽን ነው፡፡ ማሽኑ በሰዓት 20 ቶን የሚደርስ የሊቲየም ምርትን ፕሮሰስ የማድረግ አቅምም አለው፤ ለልማቱ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ማሽኖች በቀጣይም ወደ ሀገር ውስጥ ይገባሉ፡፡

ማሽኑ የሊትየም ምርትን ፕሮሰስ በማድረግ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ይህን ዘመናዊ ማሽን በመጠቀም የሚመረተው ሊትየም ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የሚያሳድግና ትልቅ ኢኮኖሚያዊ አቅም እንደሚፈጥር ሼህ አሊ አስታውቀዋል፤ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላል ብለዋል፡፡

ሼህ ዓሊ እንዳሉት፤ በዋናነት ለመኪና ባትሪ አገልግሎት የሚውለው ይህ ሊትየም የተሰኘው ማዕድን፣ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ በእጅጉ ይፈለጋል፡፡ በርካታ ሀገራትም የማዕድን ሃብቱን ተጠቅመው ማደግ ችለዋል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያም በተፈጥሮ የታደለቻቸውንና ተዝቀው የማያልቁ የተፈጥሮ ሃብቶች ያላት ሀገር እንደመሆኗ እነዚህን ሃብቶች በመለየት አውጥቶ መጠቀምና ማልማት ይገባል፤ ለዚህም ቀንጢቻ ማይኒንግ በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የሊትየም ማዕድን ፈልጎ ወደ ልማቱ የገባ ብቸኛ ኩባንያ መሆን ችሏል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ፕሮጀክቱ በ80 ቢሊዮን ብር ወጪ የተገነባ ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ ከሚጠይቀው ወጪ በበለጠ ለሀገሪቷ ይዞ የሚመጣው በረከት ትልቅ በመሆኑ ኩባንያው ለፕሮጀክቱ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያን ለማሳደግ ከተፈለገ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ የማዕድን ሃብቶችን እንደ ነዳጅና ማዕድናት ያሉትን ማልማት የግድ ነው ያሉት ሼህ ዓሊ፣ ለዚህም መንግሥትን ጨምሮ እያንዳንዱ ዜጋ ግንዛቤው ኖሮት ተባባሪ መሆን ይኖርበታል ብለዋል። ፕሮጀክቱ ማዕድኑን በማልማት ከሚፈጥረው የሥራ ዕድልና ከሚያመጣው የውጭ ምንዛሪ ባለፈ ለመላው ኢትዮጵያዊ ሃብት መሆኑንም አስታውቀዋል፤ ሀገሪቷን ወደ ላቀ የዕድገት ጉዞ የሚወስዳትና ካደጉ ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ ትልቅ አቅም ያለው እንደሆነ ነው ያስገነዘቡት፡፡

‹‹ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ዕምቅ አቅም ያላት ቢሆንም ፈልገን ያገኘነውና ለማልማት የሞከርነው እጅግ በጣም ጥቂቱን ነው›› ያሉት ሼህ ዓሊ፤ ማዕድናቱን ፈልጎ የማግኘቱ ሥራ ቀዳሚና እንደሆነና ገና ብዙ መሥራትን እንደሚጠይቅም ተናግረዋል። በአሁኑ ወቅት እየለሙና በሕገወጥ መንገድ እየወጡ ያሉ ማዕድናት ከመሬት የላይኛው ክፍል በቀላሉ የሚገኙት እንጂ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት አለመሆናቸውን ጠቅሰው፤ በሀገር ውስጥ ያሉ ማዕድናት ገና ያልተነኩና ያልተመረቱ ስለመሆናቸው አስታውቀዋል፡፡

ዘመናዊ ማሽነሪዎችን በመጠቀም ማዕድኑን ፈልጎ ለማውጣትና ለማልማት መሰል ተቋማት ወሳኝ መሆናቸውን ነው ያመለከቱት፣ ከልማቱ በተጨማሪ መሰል ኩባንያዎች በሕገወጥ መንገድ የሚወጡ ማዕድናትን ለመከላከል አቅም እንዳላቸውም ተናግረዋል፡፡

‹‹በቀጣይም ቀንጢቻ የማዕድን ፋብሪካ ከሚያመርተው ማዕድን በተጨማሪ በተለያየ መንገድ ማዕድን ከሚያወጡ አካላት ጋር በጋራ ይሠራል›› ያሉት ሼህ ዓሊ፤ ማንኛውንም ማዕድን በጥሬው ወደ ውጭ ገበያ ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ ሲላክ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያስገኝም ነው የተናገሩት። ኩባንያው በቀጣይም የተለያዩ ማሽነሪዎችን በማስመጣት እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡

ቀንጢቻን የመሳሰሉ ኩባንያዎች ሲበራከቱ ሀገሪቱ በዋናነት በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በቴክሎጂ ሽግግር ዘርፈ ብዙ በሆነ መልኩ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችልም አስታውቀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሕገወጥ መንገድ የሚወጣውን ማዕድን መከላከልና መቆጣጠር እንደምትችልም ይጠቁማሉ፡፡

‹‹ኢትዮጵያ ከማዕድን በተጨማሪ የነዳጅ ሀብት ያላት ሀገር እንደመሆኗ በነዳጅ ሀብት ልማትም እንዲሁ ጠንክሮ መሥራትን ይጠይቃል›› ያሉት ሼህ ዓሊ፤ ኩባንያው በቀጣይም በነዳጅ ሃብት ልማት ላይ የመሰማራት ዕቅድ እንዳለውም ጠቁመዋል። በዚህም ሀገሪቷንና ሕዝቧን ከድህነት ማውጣት እንደሚቻል ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህም ማኅበረሰቡ በተለይም በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚገኘው የጉጂ ማኅበረሰብ አሁን የገቡትን ማሽነሪዎች እንደ ግል ሃብቱ ተመልክቶ ሊጠብቃቸው፣ ሊንከባከባቸውና ሥራውን ሊያግዝ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡ ዘርፉ የሚያመነጨው ሃብትም ኦሮሚያን ጨምሮ ለመላው ኢትዮጵያ ፋና ወጊ ነው ብለዋል፡፡

ሊትየም ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱ ለማዕድን ዘርፉ ትልቅ ተስፋ መሆኑን የጠቀሱት የአፍሪካ ማይኒንግና ኢነርጂ ምክትል ሥራ አስኪያጅና በቀንጢቻ ማይኒንግ ሼር ያላቸው አቶ ሳሚ ሚሊዮን፣ ኩባንያው ሊትየምን ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን ይናገራሉ፤ አሁን ምርቱን ማምረት የሚያስችለውን ዘመናዊ ማሽን ማምጣት እንደቻለም ተናግረዋል፡፡ ቀንጢቻ ማይኒንግ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ያላትን ዕምቅ አቅም አውጥታ መጠቀም እንድትችል ትልቅ አቅም መሆን እንደሚችልም ተናግረዋል፡፡

ዓለም የመኪና ባትሪን እየተጠቀመ ባለበት በዚህ ወቅት ለመኪና ባትሪ አገልግሎት የሚውል ንጥረ ነገርን ማግኘት ተስፋ ሰጪና የሚበረታታ መሆኑን አቶ ሳሚ ተናግረዋል፡፡ ሊትየም በተገኘበት አካባቢ ከዚህ ቀደም ታንታለም ይመረት እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሳሚ፤ ኩባንያው ሊቲየምን ፈልጎ ወደ አካባቢው እንደሄደም አስታውቀዋል። በዚህም ሊቲየምን ማግኘት እንደቻለና ወደ ውጤት እየቀረበ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ኩባንያው በቀጣይ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥም ማሽኑን በመትከል የሙከራ ምርት ያመርታል፡፡ ኩባንያው ማሽኑን ከማስገባት ባለፈ ቴክኖሎጂውን ማሸጋገር ችሏል፤ ይህም እንደ ሀገር ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመቅረፍ ረገድ ዓይነተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን፣ በዘርፉ ትልቅ የአቅም ግንባታ መፍጠር ተችሏል፡፡

ኩባንያው ማሽኖችን ባስገባበት ወቅት የተገኙት የቀንጢቻ ማይኒንግ ኩባንያ ጀኔራል ማናጀርና ዋና ዳይሬክተር ሚስተር ብሩስ ቲኒ በበኩላቸው፤ ቀንጢቻ ማዕድን ፋብሪካ ሊትየምን ለማምረት የሚያስችሉትን ዘመናዊ ማሽነሪዎች ማስገባት እንደጀመረና በቅርቡም ወደ ምርት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ይህም ለሀገሪቷ ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ የሚኖረው ከመሆኑም በላይ ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ማኅበረሰብም ሆነ ለመላው ኢትዮጵያዊ የጎላ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ኩባንያው የማዕድን ሀብቱን ከማልማት ጎን ለጎን ለአካባቢው ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ የጤና ተቋማትና የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን እያሟላ መሆኑንም አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት ትልቅ አቅም እንዳላት ጠቅሰው፣ ሀገሪቱ በማዕድን ዘርፍ ብዙ መሥራትና መጠቀም ይኖርባታል ብለዋል፡፡ ወቅቱ የሊትየም ምርት በዓለም ላይ ተፈላጊነቱ በእጅጉ እየጨመረ ያለበት መሆኑን የጠቆሙት ሚስተር ብሩስ፤ ኢትዮጵያም በቀጣይ በሊትየም ምርት ከፍተኛ ገቢ የምታገኝበትና የውጭ ባለሀብቶችን ትኩረት መሳብ የምትችልበት ጊዜ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ቀንጢቻ ማይኒንግ በአውስትራሊያ እና በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተቋቋመ በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ የተመሠረተ ኩባንያ ሲሆን፤ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ከ1000 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር፣ ዘርፉ በተለይም በውጭ ምንዛሪ ግኝት ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተገልጿል፡፡

ከኢትዮጵያ ከርሰ ምድር የተገኘው የሊትየም ማዕድን በሙሉ አቅም መመረት ሲጀምርና ለዓለም ገበያ ሲቀርብ ኢትዮጵያ በዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ማግኘት እንደምትችልም ነው መረጃዎች ያመለከቱት፡፡

የቀንጢቻ ማይኒንግ ኩባንያ ባለበት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጉጂ ዞን ሰባ ቦሩ ወረዳ ቀንጢቻ አካባቢ እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ የታንታለም ማዕድን ክምችት በሩሲያ የጂኦሎጂ ባለሙያዎች የተገኘ ስለመሆኑና በማዕድን ክምችቱም ከታንታለም ውጪ የዩራኒየምና ሊቲየም ማዕድናት እንደሚገኙ ስለመረጋገጡ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ፍቅር ጌታ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ፀሐይ ውበታም ሴት ናት፡፡ ተፈጥሮ የአንዷትን ውብ ሴት ፈገግታ ፀሐይ አድርጎ ህዋ ላይ የሰቀላት ይመስለኛል፡፡ ዓለም የደመቀችው በፀሐይ በተሳለችው የሴት ልጅ ፈገግታ ነው፡፡ እሷን ሳይ እንዲህ ብቻ ነው የማስበው፡፡

የምሠራበት ቦታ ሰርቪስ መጠበቂያዋ ነው፡፡ እዚያ ቦታ ሊስትሮ ሆኜ መሥራት ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በሴት ውበት ነፍሴ ስትደክም እሷን ነው የማውቀው፡፡ ቦርሳዋን በእጇ አንጠልጥላ ማስቲካዋን እያላመጠች ወዳለሁበት ትመጣና የምሠራበት ወንበር ላይ አረፍ ትላለች፡፡ ለአምስት አመታት ጫማ ስጠርግ እንደ እሷ እግር ደልቶኝ እና ወድጄ የምጠርገው ጫማ የለም፡፡ ጫማዎቿ ያማምራሉ፡፡ ንጹህ ናቸው፡፡ በአየር ላይ የምትንሳፈፍ እንጂ መሬት የምትረግጥ አትመስልም፡፡ ጥረግልኝ ብላ ሊስትሮ ዕቃዬ ላይ እግሮቿን ስታስቀምጣቸው አበላሽልኝ ብላ የመጣች ነው የሚመስለኝ፡፡ እንደዚያ ንጹህ ሆነው ለምን ጥረግልኝ እንደምትለኝ ግራ ይገባኛል፡፡ በእሷ ጫማ ላይ ልዩነት ፈጥሬ አላውቅም፡፡ በሳሙናና በብሩሽ ፈትጌ አጥቤላት እንኳን ውበታቸው እንደበፊቱ ነው፡፡ እንዴትም ባጸዳላት የልቤ ደርሶ አያውቅም፡፡ ገንዘቧን ዝም ብላ የምትከሰክስ ሞኝ መሰለችኝ፡፡

ጫማዎቿ በብዛት ነጭ ናቸው፡፡ ነጭ ቀለም እንደምትወድ በጫማዎቿ ማወቅ ቻልኩ፡፡ ክፍት ጫማ ስታደርግ አይቻት አላውቅም፡፡ ማንም ሳይነግረኝ እግሯ ላይ ችግር እንዳለባት ደረስኩበት፡፡ እንደዚያ ባይሆን እማ ይሄን ሁሉ ጊዜ በሽፍን ጫማ አላያትም ነበር ስል ለራሴ ጥያቄ መልስ ሰጠሁ፡፡

ብዙ አታወራም..ትመጣና እግሯን ሊስትሮ ዕቃዬ ላይ ታስቀምጥና እንድጠርግላት ዓይን ዓይኔን ታስተውለኛለች። ስታየኝ በልቧ ነው፡፡ በልብ ማየት ከአእምሮ ርቆ ነው፡፡ እንባ ባንጠለጠሉ ዓይኖች..ሊወርድ የሚታገል እንባን አምቆ፣ የኀዘን ደመና ባጠላበት ፊት፡፡ የእናት መሳይ ዓይን አላት፡፡ እያዩ የሚያልባቸው...እያስተዋሉ የሚቃትቱ ዓይኖች፡፡

‹ለምን ታዝንልኛለች..? ከእይታዋ ጋር አብሮ የሚነሳ ጥያቄዬ ነው፡፡ ስታየኝ ሰንብታ ወደ ሰርቪሱ ትገባለች፡፡ መልካም ቀን ሳትመኝልኝ ሄዳ አታውቅም፡፡ ከሥራሁበት በለጥ ያለ ገንዘብ አስጨብጣኝ ‹መልካም ቀን› ትለኛለች፡፡ ከዚያ መልካም ምኞት በኋላ ቀኖቼ የተባረኩ ነበሩ፡፡ ቀን ሙሉ አስባታለሁ...የቀኔ ትልቁ ሃሳቤ እሷና ሀሳቧ ናቸው፡፡

ሥራ ስፈታ ወደማነበው ጋዜጣ እጄን ሰድጄ አንድ መዘዝኩ። ከሃሳቤ ጋር የተጣጣመ አንድ መልዕክት ተመለከትኩ፡፡ ከዚያች ሴት መልካም ቀን በኋላ ሁሉም ነገር አገልጋዬ ሆኗል፡፡ ጋዜጣው ላይ እንዲህ ተጽፏል..ልብ የፍቅር ቦታ ነው፡፡ ፍቅር ባህሪው እዝነት ነው፡፡ የሚያዝኑ ሁሉ ለፍቅር የተረቱ ናቸው..› ከጋዜጣው ላይ ዓይኔንም ሃሳቤንም ሰብስቤ ‹ለማያውቁት ዝም ብሎ ማዘን ይቻላል? ስል ራሴን ጠየኩ፡፡ መልሱ ሲያቅተኝ ወደጋዜጣው ማተርኩ፡፡ ከእኔ እውነት እጅግ የራቀ መልስ ጋዜጣው ርቃን ላይ ተከትቦ አነበብኩ፡፡ እንዲህ ይላል ‹ልብ የእውነት ዙፋን ነው። ዙፋኑ ለመውደድና ለማፍቀር ሰው አይመርጥም..ዝም ብሎ ማፍቀር የዚህ ዙፋንና ልብ ባህሪዎች ናቸው›

በሃሳቤ ያቺን ሴት ተከተልኳት..እኔን ባየችበት የእዝነት እይታ ሌሎችን እያየች መሆኗን ሳስብ፣ ለእኔ ባቀረሩ እናታዊ ዓይኖቿ ለሌሎች ማቅረሯን ስረዳ ልጠላት ከአፋፍ ደረስኩ። እንደእሷ መሆን ተመኘሁኝም ፈራሁም፡፡ እንደእሷ መሆን ይናፍቃል እንጂ አይደረስም የሚለው መደምደሚያ ሃሳቤ ነበር፡፡

ወደጋዜጣው ቀልቤን ሰደድኩ..ከሌላ ሃሳብ እና እምነት ጋር አላተመኝ፡፡ ‹እግዜር ሲኦልን አልሠራም፡፡ ሲኦል የሰው ልጆች የሃሳብ፣ የምኞት፣ የድርጊት መዳረሻ ነው፡፡ የላይኛው ንጉሥ ልጆቹን ይቅር እያለ የሚኖር አባት ነው፡፡ ንጹህ እጁ በሲኦል አትቆሽሽም፡፡ ሲኦል ከእግዜር የሸሹ አእምሮና ልቦች የሚገኙበት የቅጽበት ድሎት ነው፡፡ ሌሎችን አለማፍቀር የሚፈጥረው የህመም ውጋት የነዚህ አእምሮና ልቦች ዘላለማዊ እዬዬ ነው›

ዝም አልኩ..በጽኑ፡፡ አንድ የጫማ ደንበኛዬ ፊቴ ቆሞ እስካስደነበረኝ ጊዜ ድረስ ከነዝምታዬ ነበርኩ፡፡ ለማታውቀው ለእኔ እንባ ያቀረሩ ዓይኖች ያሏትን ሴት በብርቱ ናፈኩ፡፡ ፍቅሬን ከዚህ ደንበኛዬ በመጀመር ልቤን የእዝነት ዙፋን ለማድረግ ማንም አልቀደመኝም ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥርስ በጥርስ ሆኜ የወዳጄን ጫማ ጠረኩ፡ ፈገግታዬ ደንበኛዬን ያስገረመ ይመስላል። ‹ዛሬ ደስተኛ ሆነህል ምን ተገኘ?

‹ሲኦል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? አልኩት ከነሳቄ፡፡

‹አላውቅም..ግን የመከራ ቦታ፣ የክፉ ነፍሶች ማረፊያ› ይመስለኛል፡፡

ከመናገሬ በፊት ዝምታ ቀደመኝ፡፡ በደንበኛዬ ንግግር ‹ሰው ሁሉ ገብቶት የሚኖር ነው አልኩ፡፡ ግን የገባውን ያክል የሚኖር ሰው ባለማግኘቴ ግርምቴ ጣሪያ ተሻግሮ ሰማይ ነካ። ብዙዎቻችን ብዙ እናውቃለን ያወቅነውን ስንኖር ግን አንታይም፡፡ ማወቅ እውነትን ካልሰጠን ካለማወቅ የበረታ ስቃይ ነው የሚል አባባል ታወሰኝ፡፡

‹ምነው ዝም አልክ? ›የደንበኛዬ ድምጽ ተሰማኝ፡፡

‹አይ እንዲሁ ነው› አልኩት፡፡ ሁሉንም ትቼ ወደሳቄ ተመለስኩ፡፡ የማውቀውን ልኖር፣ ያላወኩትን ልጠይቅ አሁንን መረጥኩ፡፡ አንዷት ነፍስ ከነሃሳቧ ናፈቀችኝ፡፡

ከመቀመጫው እየተነሳ ‹ሁለት ብር ይጎድለኛል ሌላ ጊዜ እሞላልሃለሁ› ሲለኝ ከዝምታዬ እየባነንኩ ነበር፡፡ በዚህ ሰው ዛሬ ከነጋ..ከነጋ አልኩ ከመጣ ሦስት ጊዜ መበርገጌ ነው። ለማስደንገጥ የተፈጠረ መሰለኝ፡፡ ነው እኔ እሆን ለመደንገጥ የቀረብኩት? ጣቶቼን ወደሌሎች መቀሰሬን ትቼ ራሴን መፈተሽ ጀመርኩ፡፡ እውነት ነው እኔ ነኝ ለመደንገጥ የቀረብኩት፡፡ በዝምታ ተለጉሜ ራሴን ለድንጋጤ ባላመቻች ኖሮ በዚህ ሰው ንግግር ባልደነገጥኩ ነበር፡፡ እናም ጥፋቱ የኔ ነው አልኩ፡፡ የማውቀውን ለመኖር ቃል ገብቼ የለ? ራሴን ተጠያቂ በማድረግ እውነትን ጀመርኩ፡፡

ሁለት ብር የጎደለውን ፍራንክ ዘረጋልኝ፡፡

‹ዛሬ በእኔ ወጪ ነው..ዘና በል አልኩት..

‹ምን ተገኘ? አለኝ፡፡

‹ሰዎችን ለማስደሰት አዲስ ነገር አያስፈልግም፡፡ ያለኝን ስቆጥር የሊስትሮ ባለሙያ ሆኜ ራሴን አገኘሁት እናም ባለኝ ነገር ሰዎችን ላስደስት ተነሳሁ፡፡

‹አመሰግናለሁ..› አለኝ፡፡

በሳቄ እጅ ነሳሁት፡፡

‹መልካም ቀን› ብሎኝ ሲሄድ ግን በታላቅ መገረም ውስጥ ነበርኩ፡፡ እስከዛሬ ወደእኔ በተመላለሰባቸው ማለዳዎች እና ከሰዓቶች ውስጥ አንድም ቀን ‹መልካም ቀን› ብሎኝ አያውቅም ነበር፡፡ ሳቄ በፊቴ ላይ ኀመራ፡፡ በሰማይ ርቃን ላይ እንደሚጥመለመል የሙብረቅ ፍላጻ ፊቴ በብዙ ፈገግታ ፈካ። ተቀይሬ የቀየርኩት መሰለኝ፡፡ መሰለኝ አይደለም ነው ስል ደመደምኩ፡፡ ለዘላለም በማውቀው ፊቱ ላይ ያላስተዋልኩት ፈገግታና በጎ ቃል በእኔ ካልሆነ በማን መጣ? ያ በምንም የሚፈግ የማይመስለው ቁጡ መሳይ ፊቱ ርህራሄን ለብሶ ሲሄድ ከእኔ ውጪ ማን ተጠያቂ ሊሆን ይችላል? ለመጀመሪያ ጊዜ በራሴ ኮራሁ፡፡

ጀምበር ሸሸች..ጠዋት ሆነ..

ሰርቪስ ከሚጠብቁ ሴቶች መሀል ቦርሳዋን በእጇ ያንጠለጠለች አንድ ሴት ፈለኩ አላገኘሁም፡፡ እንዲህ የምታረፍድበት አንዳንድ ጊዜዎች አሉ፡፡ ከነጋ አልቆየም የቀደመኝ ለማኝ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ሌሊት ቀረች ብዬ መስጋቴ ራሴን እንድጠራጠረው አደረገኝ፡፡ እንዲህ አስቤ አላቆየሁም። ተሻግሮ ካለው አስፓልት መኪና ለማሳለፍ ቆማ አየኋት፡፡ የጀመርኩትን ጫማ ለመጨረስ ዝቅ ባልኩበት ሰሞን ‹ከእንዴት አደርክ ጋር አንድ ሂል ያደረገ እግር ሊስትሮ ዕቃዬ ላይ ሲያርፍ አንድ ሆነ። ቀና ስል እሷ ናት..የቋጠርኩት ፈገግታ ያለ ይመስል እንዳየኋት ደስታዬን ለቀኩት፡፡ እሷን በተመለከተ ብዙ የተሳሳትኩት ነገር እንዳለ በእግሮቿ ውበት ነበር ያመንኩት፡፡ ከትናንት በፊት ያለው እኔ አሳቀኝ፡፡ ዛሬ ብቻ አይደለም ሁሌም የምስቅበትን እኔ አሻግሬ ተመለከትኩት፡፡ ሳያይ የሚፈርድ፣ በይሆናል የሚኖር ሆኖ አገኘሁት፡፡

በውበት ያጌጡ እግሮቿን ሊስትሮ ዕቃዬ ላይ ሳያቸው ልታርፍ መስሎኝ ዝም አልኩ፡፡

‹ሰርቪስ እንዳያመልጠኝ..›

ስትለኝ..እንድጠርግላት የፈለገች መሰለኝ፡፡ ምኑን እንደምጠርግ ግራ ገባኝ፡፡ እግሮቿም ጫማዎቿም ንጹህ ናቸው። ለመጥረግ እንዲመቸኝ ይመስለኛል..ነው እንጂ ከዚች ደግ ሴት ልብ ውስጥ ከዚህ ወዲያ ምን ይታሰባል? ቁርጭምጭሚቷ ላይ ያረፈ ሱሪዋን ወደ ላይ ሳበችልኝ፡፡ ከማልቋቋመው ባቷ ጋር ተፋጠጥኩ። በጥልፍልፍ ሂል ውስጥ ጣቶቿን አየኋቸው። በውበት እና በማማር የአራስ ልጅ ጣቶች ይመስላሉ..፡፡ ቀይ ባት.. ከረጃጅም ጣቶች እና ከተስተካከሉ ጥፍሮች ጋር..የቀኔ ምርጥ ገጠመኝ ሆኖ አለፈ፡፡

‹ካላፈቀሩበት ልብ ሲኦል ነው..ሞቶ የሚገል› የሚል ከየት እንደመጣ የማላውቀው ሃሳብ ወደአእምሮዬ ሰተት አለ። ቀና ብዬ አየኋት በነዛ ፊቴ ሲቀርቡ በሚያዩኝ አዛኝ ዓይኖቿ ስታስተውለኝ እጅ ከፍንጅ ያዝኳት፡፡

አንድ ጥያቄ አለመጠየቅ አልቻልኩም..፡፡ ልጠይቃት አፌን ሳሞጠሙጥ ወዲያው መልሱ ልቤ ውስጥ ተፈጠረ፡፡

ጥያቄዬ..

‹ጉድፍ ያልነካቸውን አዲስ ጫማዎችሽን እንድጠርግልሽ ወደእኔ የምትመጪው ስለምን ነው?

መልሱ..

የገባህ ስለገባኝ..

# ዓለም አቀፍ



## ታይዋን በራሷ አቅም የሠራቻቸውን ባህር ሰርጓጅ መርከቦች ይፋ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ታይዋን በራሷ አቅም የሠራቻቸውን ባህር ሰርጓጅ መርከቦች ይፋ አደረገች።

የታይዋን ፕሬዚዳንት ሳይ ኢንዌን የደሴቷን የመከላከያ አቅም ያጠናክራሉ የተባሉትን ባህር ሰርጓጅ መርከቦች አስተዋውቀዋል።

ፕሬዚዳንቷ በይፋ ያስተዋወቋቸው ስምንት ባህር ሰርጓጅ መርከቦች በሁለት አመት ውስጥ ወደ ሥራ እንደሚገቡም ነው የተገለጸው። «ከዚህ በፊት በሀገር ቤት ባህር ሰርጓጅ መርከቦችን መሥራት የማይቻል ይመስል ነበር፤ አሁን ግን በራሳችን አቅም ዲዛይን ተደርገው የተሠሩ መርከቦችን በዓይናችን መመልከት ችለናል» ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳይ ኢንግዌን።

መርከቦቹን መሥራቱ የራሱ ፈተና ቢኖረውም የደሴቷን ራስን በመከላከያው ዘርፍ የመቻል ጥረት ለማሳካት መሰል እርምጃዎችን መውሰድ የግድ መሆኑንም ነው ያነሱት። ታይዋን በ1980ዎቹ ከኔዘርላንድስ የገዛቻቸውን ሁለት ባህር ሰርጓጅ መርከቦችን የሚቀላቀሉት አዳዲሶቹ ታይዋን ሠራሽ መርከቦች የደሴቷን የባህር ኃይል ይበልጥ እንደሚያጠናክሩ ይጠበቃል።

ታይፒ የባህር ሰርጓጅ መርከቦቹን በመሥራት ረገድ ከተለያዩ ሀገራት ልምዶችን መቅሰሟን ብትገልጽም የትኞቹ ሀገራት ድጋፍ እንዳደረጉላት ግን አልጠቀሰችም። የታይዋን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆሴፍ ው በታይፒ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ከቻይና የሚደርሰው ጫና እየተበራከተ መሄዱንና የደሴቷን ወታደራዊ አቅም ማሳደጉ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን አብራርተዋል።

ታይዋንን እንደ ሉዓላዊ ሀገር በመቁጠር የመሣሪያ ሽያጭ ያጸደቀችው አሜሪካ የባህር ሰርጓጅ መርከቦቹ በይፋ ሲተዋወቁ ባለሥልጣኗን መላኳን ሬውተርስ አስነብቧል።

ታይፒ ሚሳኤል የሚታጠቁትን ባህር ሰርጓጅ መርከቦች ከ2025 ጀምሮ ወደ ሥራ ለማስገባት አቅዳለች። እያንዳንዳቸው 1 ነጥብ 53 ቢሊዮን ዶላር ያወጣሉ የተባሉት መርከቦች ጥቃት ለማድረስ የአሜሪካውን ሎክሄድ ማርቲን ኩባንያ ቴክኖሎጂ እንደሚጠቀሙ ተገልጿል።

ባህር ሰርጓጅ መርከቦቹ በቀጣይ ወር ሙከራ እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን፥ ቤጂንግ እስካሁን ስለአዳዲሶቹ መርከቦች መግለጫ አላወጣችም። በተያያዘ ቻይና የሉዓላዊ ግዛቴ አካል ናት ወደምትላት ታይዋን በየዕለቱ የጦር ጄቶቿን እየላከች መሆኑን ታይፒ ገልጻለች ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።



ሞዴል ኤ የተሰኘው በራሪ ተሽከርካሪ በ 280 ሺህ ዶላር ስገበያ እንደሚቀርብ ተገልጿል

## የአሜሪካው የቴክኖሉጂ ኩባንያ በራሪ ተሽከርካሪ መሥራቱን ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካው የቴክኖሎጂ ኩባንያ በራሪ ተሽከርካሪ መሥራቱን ገለጸ

በየዘመኑ የተፈበረኩ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች የሰው ልጆችን ሕይወት ሲያቀሉ ቆይተዋል። የሰው ልጆች ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመው እስከ ጠፈር ድረስ ተጉዘው ማሰስ መቻላቸው፣ የኢንተርኔት አገልግሎት እና አሁን ደግሞ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን እየተገለገሉ ይገኛሉ።

ከዚህ በፊት በቢሆኔ ፊልሞች ላይ ሲታዩ የነበሩ የበራሪ ተሽከርካሪ አገልግሎት እውን ሊሆን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል።

ዋና መቀመጫውን በአሜሪካ ካሊፎርኒያ ያደረገው አሌፍ ኤሮናውቲክስ የቴክኖሎጂ ኩባንያ አዲስ ፈጠራውን ይዞ ብቅ ብሏል። ይህ ኩባንያው ከሰሞኑ በዲትሮይት የአውቶሞቲቭ አውደ ርዕይ ላይ ለእይታ ያቀረበው በራሪ ተሽከርካሪ የብዙዎችን ትኩረት ስቧል። ይህ በራሪ ተሽከርካሪ ከአሜሪካ አቪዬሽን አስተዳደር ፈቃድ ያገኘ ሲሆን የሙከራ በረራውን በቅርቡ እንደሚያጠናቅቅ ዩሮ ኒውስ ዘግቧል።

ሞዴል ኤ የሚል ስያሜ የተሰጠው ይህ በራሪ ተሽከርካሪ በኤሌክትሪክ እንደሚሠራም ተገልጿል። ኩባንያው የሙከራ በረራውን በአየር ላይ በ320 ኪሎ ሜትር በምድር ላይ ደግሞ በ160 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ ያደርጋልም ተብሏል።

ኩባንያው ከአንድ ዓመት የሙከራ በረራውን አጠናቆ በ2025 ለዓለም ገበያ በ280 ሺህ ዶላር ዋጋ እንደሚቀርብ ተገልጿል። የአየር ላይ ታክሲዎች በሌሎች ሀገራትም እየተሠሩ ሲሆን የጀርመኑ ቬሎኮፕተር የመጀመሪያ ምርቱን ከአንድ ዓመት በኋላ በሚካሄደው ፓሪስ ኦሎምፒክ ላይ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ተብሏል።

የአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ ምሁራን በበኩላቸው የተሽከርካሪዎቹ ዋጋ ውድ መሆን፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ገና አለመጀመሩ ለበራሪ ተሽከርካሪ ኢንዱስትሪ ዋነኛ ፈተና ይሆናሉ ብለዋል ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ከትናንት ያደሩ ወረቶቻችን የዛሬ ስንቆቻችን ናቸው

እስማኤል አረቦ

**ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው። ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣልን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሉናል። በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፣ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው**

ሀገር በአንድ ጀንበር ተገንብታ አታድርም፡፡ ትናንት ለዛሬ አሻግሮ በሚሰጠውና ዛሬም በተራው በሚያቀብለው ወረት ነው ሀገር እየተገነባች የምትጓዘው፡፡ በአጭር አማርኛ ዛሬ ያለትናንት የለም፤ ነገም ያለ ዛሬ ህልውና የለውም፡፡

አዲስ የገባው 2016 ዓ.ም ያለ 2015 ዓ.ም እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በ2015 በበጎም ሆነ በክፉ የተከሰቱ ጉዳዮች በ2016 ዓ.ም በበጎም ሆነ በክፉ ዐሻራ ማሳረፋቸው አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህም በ2015 ዓ.ም እንደሀገር ያገኘናቸው ድሎችና ያጋጠሙን ተግዳሮቶች አዲስ በያዝነው አመት ላይ የራሳቸውን ዐሻራ ማሳደራቸው አይቀሬ ነው፡፡

እንደ ሀገር የነበሩን ጥንካሬዎች ለመጪው ጊዜ እርሾ ሆነው ያበረቱናል፤ ድክመቶቻችንም እንዲሁ ታርመው ለነገ ጥንካሬያችን ምንጭ ይሆኑናል። በአጠቃላይ ጥንካሬዎቻችንን አጎልብተን፤ ድክመቶቻችንን ቀርፈን የተሻለች ሀገር እንደትኖረን እንደ መልካም ዕድል ሆነው ያገለግሉናል፡፡

የሸኘነው 2015 ዓ.ም እንደሀገር በርካታ ውጤቶች ያገኘንበትና በዚያው መጠንም የተፈተንንበት አመት ነው፡፡ በ2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ጎልታ የወጣችበት፤ በግብርና ምርት ውጤት ያመጣችበት፤ የድሆችን እንባ ያበሰችበትና ሰላምንም ለማጽናት ብዙ ርቀት የተጓዘችበት ነው፡፡

ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት አመታት ሲካሄድ የነበረው ደም አፋሳሽ ጦርነት የቆመበትና የፕሪቶሪያው ስምምነት የተፈረመበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ የፕሪቶሪያ ስምምነት ኢትዮጵያውያን ያለማንም ጣልቃ ገብነት የሀገራቸውን ሰላም ማስጠበቅ እንደሚችሉ ያሳየና በዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድም ግርማ ሞገስን ያላበሰ ታሪካዊ ክንውን ነው፡፡

ይህም ስምምነት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረውን ጦርነት አስተማማኝ በሆነ መልኩ የቋጨና ሞት፤ የአካል መጉደል፤ ስደትና መፈናቀልን በማስቀረት ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ልማት እንድትመልስ ያስቻለ ነው፡፡ ይህ ስምምነት ኢትዮጵያውያን የጦርነት ብቻ ሳይሆን የሰላም ጀግኖች እንደሆኑ ያሳየና በሀገሪቱ ታሪክም አዲስ ታሪክ እንዲጻፍ ያስቻለ ነው፡፡

2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ጎልታ የወጣችበት አመት ነበር ማለትም ይቻላል። በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ፣ ከተደረገው የሰላም ስምምነት በመከተል ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ከአውሮፓ ሀገራት ጋር ተቀዛቅዞ የነበረው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ መቀጠል መጀመሩ በዓመቱ ከተከናወኑ ዓበይት የዲፕሎማሲ ድሎች መካከል የሚዘከር ነው፡፡

ከዲፕሎማሲያዊ ድሎቹ መካከል ተጠቃሽ የሆነው አንዱ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊነትን ከያዙ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ያደረጉት አንቶኒ ብሊንከን፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርን ጨምሮ ከተለያዩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ስለሀገራቱ ቀጣይ ግንኙነት መወያየታቸው ነው፡፡

ሌላው ተጠቃሽ የሚሆነው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በጣሊያን ሮም በተካሄዱ የተባበሩት መንግሥታት የልማትና ፍልሰት ጉባዔ እንዲሁም የዓለም ምግብ ድርጅት የምግብ ሥርዓት ስብሰባ ላይ ተሳትፈው ኢትዮጵያ በምግብ ራስን በመቻልና ሕገ ወጥ ስደትን በመከላከል በኩል ያላትን ልምድ ማካፈላቸው ነው፡፡ ከጉባዔው ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ውይይትም አድርገዋል፡፡

የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት አጃይ ባንጋ ባሳለፍነው አመት ኢትዮጵያ በመምጣት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተነጋግረዋል፡፡ የፕሬዚዳንቱ ጉብኝትም የዓለም ባንክ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የትብብር አድማስ በማስፋት ለኢኮኖሚ እድገታችን በኮንሴሽናል ፋይናንስ፣ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን በኩል ጠንካራ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ አቅርቦት በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬቶች ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት አዲስ አበባ መጥተው 17 ስምምነቶችን የተፈራረሙትም በዚሁ ዓመት ነው፡፡

በሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 569 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል ዓለምን በአዲስ ታሪክ ጉድ ያሰኙት በዚሁ አመት ነው፡፡ እንደ ሀገርም ባለፉት አራት አመታት ከ31 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል በበረሃማነትና በአየር ጸባይ ለምትሰቃየው ዓለማችን መድህን መሆን ችለናል፡፡

ስንዴ ከራስ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም የቀረበው በዚሁ በሸኘነው 2015 ዓ.ም ነው። በዚህ አመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡ የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው። በሩዝ ዘርፍም እየተከናወነ ያለው ተግባርም ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይነት ወደ አስመጪነት የሚያሸጋግራት ነው፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክ በትኩረት በመሥራት ላይ ትገኛለች። በተለይም ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተውም፤ በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በሩዝ መልማት የሚችል መሬት ቢኖርም በየዓመቱ ከ200 ሺህ ቶን በላይ ሩዝ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ 200 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ታደርጋለች፡፡

በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሥርዓት መተግበር ከጀመረ ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ መንግሥት ፊቱን ወደ ሩዝ ምርት በማዞር በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል፡፡

አሁን ላይ ሩዝ በስፋት የሚመረተው በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ትግራይ ክልሎች ሲሆን በዘንድሮው 2015/2016 የምርት ዘመን በአማራ 150 ሺህ ሄክታር መሬት በሩዝ በመሸፈን 8 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው።

በተመሳሳይም በኦሮሚያ ከ1ሚሊዮን ሄክታር በላይ በሩዝ ለመሸፈን ታቅዶ እስካሁን 700ሺ ሄክታሩን ማሳካት ተችሏል፡፡ የሁለቱ ክልሎች እንቅስቃሴ ብቻ በሀገር ውስጥ ለምግብ ፍጆታነት የሚጠበቀውን ከ6ሚሊዮን ያልበለጠ ፍላጎት በመሸፈን ቀሪውን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ነው፡፡

የ2015ዓ.ም ትሩፋቶች ከሆኑት ውስጥ የዓባይ ግድብ አራተኛ የውሃ ሙሌት ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ ትውልድ ጠንሳሽነት ግንባታው በመገባደድ ላይ የደረሰው የዓባይ ግድብ በርካታ ፈተናዎችና አሜከላዎች ቢገጥሙትም በዚህ ትውልድ አይበገሬነት ዛሬ ከራስ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት ብርሃን መሆን ችሏል፡፡ በ2105 ዓ.ም በተሠሩ ሥራዎችም በያዝነው አመት ተጨማሪ አምስት ተርባይኖችን ወደ ሥራ የማስገባት ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በአጠቃላይም በዚህ አመት ብቻ ሰባት ተርባይኖች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

በ2015 ዓ.ም እንደ ሀገር ከተገኙ የዲፕሎማሲ ስኬቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆን መቻሏ ነው፡፡ በተሠሩት እልህ አስጨራሽ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ብዙዎች የተመኙትን የብሪክስ አባልነት ኢትዮጵያውያን ማሳካት ችለዋል፡፡ ይህም ለሀገሪቱ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ይዞ የሚመጣ ነው፡፡

የለውጡ መንግሥት ሀገሪቱን መምራት ከጀመረ ወዲህ እየጎለበቱ ከመጡ መልካም ተግባራት መካከል መረዳዳትና መደጋገፍ አንዱ ነው፡፡ በተለይም ጧሪ እና ደጋፊ የሌላቸውን ወገኖች አንዱ ባህል እየሆነ የመጣ መልካም ተግባር ነው። ይህም የበጎ ፈቃድ ሥራ በ2015 ዓ.ም ተጠናክሮ የቀጠለበት አመት ነበር።

የ20ሺ አቅመ ደካማ ቤቶች ታድሰው በአዲሱ አመትም ቤት ለእንቦሳ ተብለዋል፡፡ ብዙዎችም በማዕድ ማጋራትም አዲሱን አመት ተደስተው ውለዋል፡፡ በአዲሱ አመት ዋዜማ የአዲስ አበባ አስተዳደር ብቻውን ከ450ሺ በላይ ለሚሆኑ አቅመደካሞች ማዕድ አጋርቷል፡፡

በ2105 ዓ.ም የሀላላ ኬላ የቱሪስት ማዕከል ተገባዶ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡ የኮይሻ፣ የጎርጎራ፣ የወንጪ፣ የቱሪስት መስህቦች እየተገባደዱ ነው፡፡ በአዲስ አበባም እየተከናወኑ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች መጪው ጊዜ ብሩህ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም በሀንጋሪ ዋና ከተማ ቡዳፔስት በተዘጋጀው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በዘጠኝ ሜዳሊያ ከዓለም ስድስተኛ ሆና አጠናቃለች፡፡ በሴቶች 10ሺህ ሜትር ውድድር አትሌቶቻችን ከአንድ እስከ ሦስት ተከታትለው በመግባት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች «አረንጓዴ ጎርፍ» በሚል የሚታወቁበትን የአጨራረስ ስልት ዳግም በማሳየት አኩርተውናል፡፡

በዚህ ውጤት ጉዳፍ ፀጋይ ወርቅ፣ ለተሰንበት ግደይ ብር እንዲሁም እጅጋየሁ ታየ ነሐስ አምጥተዋል። በሴቶች ማራቶን ደግሞ አማኔ በሪሶ እና ጎተይቶም ገብረሥላሴ ተከታትለው በመግባት የወርቅ እና ብር ሜዳሊያ አግኝተዋል። በወንዶች 10 ሺህ ሜትር ውድድር ሰለሞን ባረጋ ሦስተኛ በመውጣት ለሀገሩ የነሐስ ሜዳሊያ ሲያስገኝ፤ በሴቶች 1500 ሜትር ድርቤ ወልተጂ ሁለተኛ ሆና የብር ሜዳሊያ አስገኝታለች።

በወንዶች 3 ሺህ ሜትር መሰናክል የዓለም ክብረ-ወሰን ባለቤቱ ለሜቻ ግርማ ሁለተኛ ሆኖ በማጠናቀቅ ብር ማግኘት ችሏል። በመጨረሻው ቀን በተካሄደ የወንዶች ማራቶን ልዑል ገብረሥላሴ ሦስተኛ ሆኖ በማጠናቀቅ ነሐስ አግኝቷል። ኢትዮጵያ በጠቅላላው ዘጠኝ ሜዳሊያዎችን ሰብስባ ከአፍሪካ ሁለተኛ ከዓለም ስድስተኛ ሆና አጠናቃለች።

ከእነዚሁ ስኬቶች ጎን ለጎን ጦርነት፣ ግጭት፣ መፈናቀል፣ ስደት፣ ድርቅ፣ የመሳሰሉት ችግሮች ኢትዮጵያን ፈትነዋታል፡፡ አለመተማመን፣ መወነጃጀል፣ጥላቻና ቂምም የፖለቲካችን አንዱ መለያ ሆኖ አብሮን ቆይቷል፡፡ ይህም ሁኔታ በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጦርነት እንዲቀሰቀስ፣ግጭት እንዲበራከት፣ ሞትና የንብረት ውድመት እንዲከሰት አድርጓል፡፡ በዚህም በርካቶች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፣ተሰደዋል፡፡

ይህ ታሪክ ግን አንድ ቦታ ማብቃት አለበት። የሕዳሴ ግድብን የገነቡ ክንዶች፣በአንድ ጀንበር ከ569 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን የተከሉ እጆች፣የተራቡና የታረዙ ወገኖችን የታደጉ ስብናዎች ለግጭትና ለጦርነት ቦታ ሊኖራቸው አይገባም፡፡

ስለዚህም የመገጫጨት፣ የመጠፋፋት እና የመገዳደል ታሪካችን ሊዘጋ ይገባል፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፣ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው። ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል፡፡ የሥልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና፡፡ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣልን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል፡፡ በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፣ ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው፡፡

የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

# ስፖርት




## የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በዚህ ከቀጠለ ሊሰረዝ ይችላል

**አስማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር ባካሄደው አምስተኛ መደበኛ ፤ ሦስተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ዙሪያ ትናንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል። በርካታ ጉዳዮች እንደተነሱበት የተነገረው ጉባኤው የክለብ ላይሰንሲንግ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው በመግለጫው ተጠቁሟል።

በዘልማድ ትኩረት ሳንሰጥ ቆይተናል መስፈርቱን አሟልተን የማንገኝ ከሆነ ክለቦቻችን በአፍሪካ መድረክም የመሳተፍ ፈቃድ ላይኖረን ይችላል ሲሉ የሊግ አክሲዮን ማኅበሩ ፕሬዚዳንት መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ አሳስበዋል። ደረጃውን የጠበቀና ፍቃድ ያለው ክለብ ባለመኖሩም ማሟላት ግድ እንደሚል ተናግረዋል።

ክለቦች በዚህ አመት የግዴታ የክለብ ላይሰንሲግ (የክለብ ፈቃድ) ማውጣታቸው አስፈላጊ መሆኑን የጠቆሙት የሊግ ካምፓኒው ሥራ አስኪያጅ አቶ ክፍሌ ሰይፈ ለዚህ ድጋፍ እንደሚያደርጉ የገለፁ ሲሆን ክለቦች አስፈላጊውን ፍቃድ ካላሟሉ ሊጉ ሊሰረዝ እንደሚችል ስጋታቸውን አፅእኖት ሰጥተው ተናግረዋል። «መስፈርቱን አሟልተን የማንገኝ ከሆነ ክለቦቻችን በአፍሪካ መድረክም የመሳተፍ ፈቃድ ላይኖረን ይችላል» ሲሉም መቶ አለቃ ፈቃደ አሳስበዋል።

የክለቦች የሕክምና ቡድንን በተመለከተ በወጌሻ ብቻ እንደማይቀጥሉ የገለፁት አቶ ክፍሌ የሊግ ስታንዳርድ ያሟላ የሊጉ የሕክምና ቡድን ማኑዋል እንዲዘጋጅ ስምምነት መደረሱን አስረድተዋል። የፀጥታ ችግር ለውድድሩ እንቅፋት እንዳይሆን ከፌዴራል ፖሊስ ጋር የውል ስምምነት ለማድረግ መወሰኑንም አክለዋል።

ከፀጥታ ጋር ተያይዞ አስተያየታቸውን የሰጡት መቶ አለቃ ፈቃደ «የግል የፀጥታ ኃይሎች ለእኛ አስተማማኝ አይደሉም ... የሀገሪቱን ደህንነት የሚያስጠብቀው ፌዴራል ፖሊስ በመሆኑ ከነሱ ጋር ተፈራርመን ወደ ሥራ መግባትን መርጠናል፣ ሊጉ ከስጋት ነፃ ሆኖ ውድድር ማካሄድ እንደምንችል ዲ.ኤስ.ቲቪ ማረጋገጥ ይፈልጋል፣ ይህን የሚያረጋግጠው ደግሞ ፌዴራል ፖሊስ ነው። በቀጣይ መጠጥ ጠጥቶ የገባን 500 ብር ቢቀጣ የተጣላ ደግሞ ሳምንት ትታሰራለህ የሚለው መጠነኛ ፍ/ቤት ሊቋቋም የሚችለው ሁሉ በፌዴራል ፖሊስ ነው» ሲሉ አስረድተዋል።



ክለቦች ከፍቃድና ከደመወዝ ክፍያ ጋር በተያያዘ አደጋ ውስጥ እንደሚገኙ ተገልጿል፣

ከፌዴሬሽኑ ጋር ስላላቸው የሥራ ግንኙነት በተመለከተ ሲያብራሩም ትልቅ ልዩነት የተከሰተው በለገጣፎ ለገዳዲ ፎርፌ ዙሪያ ላይ መሆኑን አምነው አሁን ላይ ግን መግባባት ላይ መደረሱን አስረድተዋል። «ከፌዴሬሽኑ ጋር የየድርሻችንን ኃላፊነት ወስደናል የሚያገናኘንና የሚለየንን ለይተን ተወያይተን ተስማምተናል..በቀጣዩ ሳምንት እንፈራረማለን» ሲሉም ገልጸዋል።

መስከረም 20 የሚጀምረው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ውድድር የተሻለ የውድድር ዓመት ለማሳለፍ ዝግጅት መጠናቀቁ የተጠቆመ ሲሆን፣ ሊጉ የሚካሄድበት አዳማ ከተማ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁም ሲዳማ ቡና ከኢትዮጵያ ቡና በሚያደርጉት ጨዋታ በይፋ ይጀምራል።

በሊጉ ክለቦች የእግር ኳስ ክህሎትን ከማሳደግ ይልቅ ማጭበርበሮቹ ከፍተኛ መሆናቸውን የተናገሩት አቶ ክፍሌ፣ እሳቸው ሥራ አስኪያጅ ሆነው ከመጡ ጀምሮም ማጭበርበሩ እንደቀጠለና ይህን ለማስተካከል ከሕግ ይልቅ አስተሳሰብን መቀየር ወሳኝ እንደሆነ ገልፀዋል። ይህን ለማስተካከል ሊግ ካምፓኒው የሁሉንም ክለቦች አሠልጣኞችና ቡድን መሪዎች ጠርቶ የማጭበርበር ድርጊት እንዳይከሰት አሳስቦ ነበር። በዚህም ከዳኞች መሃል ያሠለጠኑ፣ ያስተማሩ፣ ልምድ ያላቸውን በምስጢር አዋቅሮ የነበረ ቢሆንም የተገኘ ለውጥ ግን አልነበረም። ስህተቱ ዳኞች፣ አሠልጣኞችና ተጫዋቾች እያለ ወረደ፣ አሁን ግን ከሕጉ ጎን ፕሮፌሽናል አስተሳሰብ መያዝ እንዳለበት ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል። መቶ አለቃ ፍቃደ በበኩላቸው፣ አንድ የጨዋታ ዳኛ ቡድኖችን ከአቅም በታች ተጫውተዋል ለማለት የሚያስችለው ሕጎች እንደሌሉ ጠቁመው ሲዳማ ላይ የታየው የተራቀቀ መላቀቅ እየታወቀ ሊግ ካምፓኒው የሕግ መብት ስለሌለው ምንም ማድረግ እንዳልቻለ አስታውሰዋል።

እጅግ እየናረ የመጣውን የተጫዋቾች ደመወዝ ክፍያ አስመልክቶ መቶ አለቃ ፈቃደ ማብራሪያ ሲሰጡም፣ «በደመወዝ ክፍያ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽና ኢትዮጵያ ከአንድ እስከ ሦስት ያለውን ደረጃ ይዘዋል፣ በኳሱ እድገት ግን ሰማይና ምድር ነን» በማለት ተናግረዋል።

እንደ መቶ አለቃ ፈቃደ ማብራሪያ፣ ክለቦቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተጫዋቾችና ለአሠልጣኝ ከፍተኛ ደመወዝ ተከፍሎ እግርኳሱ እየተጎዳ ነው። «አንድ በሉን ብለው ሲጠይቁን አድራጊው እነሱ ሆነው እንዴት ጠየቁን ብለን ተገርመናል፣ ዘንድሮ ሰሜን ከፍተኛ ገንዘብ ካወጣ በቀጣይ አመት ሰሜኑ ያወጣል ዝርፊያው በየተራ ይመስላል ምክንያቱ ደግሞ ዋንጫ ለማምጣት ይሉናል፣ ዋንጫ በገንዘብ አይመጣም አሁንም ክለቦቹ ተያይዘው ወደ ገደል እየሄዱ ነው» በማለትም የጉዳዩን አሳሳቢነት አስረድተዋል።

«ከደመወዝ ክፍያ ጋር ክለቦቻችን በአማካይ ለደመወዝ የምናውለው ከ45 ሚሊዮን ብር በላይ ነው ብለዋል፣ ይሄ ግን ልክ አይደለም ለወደፊቱ 99 በመቶ ለደመወዝ አውሎ መቀጠል የለም አደብ የሚያስገዛ ሕግ እናወጣለን፣ ለአሁኑ ግን በጉባኤው በከፍተኛ ደመወዝ ተጫዋች ቀጥራችሁ ሩብ አመት ሳይሞላ ደመወዝ መክፈል ያቅታችኋል፣ በዚህ ዓይነት ውድድሩ እንደሚጨረስ ምን ማስተማመኛ አለን ብለን አልጠየቅንም፣ መክፈል ያልቻለ ክለብ ነጥብ እንቀንሳለን ብለን የምንቀጣበት ሕግም ደግሞ የለም» ሲሉ መቶ አለቃ ፍቃደ የሕግ ክፍተቱን ገልጸዋል።

ስለ ደመወዝ ክፍያ ገደብ የተጠየቁት ፕሬዚዳንቱ «የ50 ሺ ብሩ የደመወዝ ገደብ ድጋሚ እንዲነሳ አንዳንዶቹ ክለቦች ይፈልጋሉ፣ ከዚህ በፊት ክለቦችና ባህልና ስፖርት ሚኒስቴሩ ቁጭ ብለው ገደቡን ወስነዋል ይሄን ለማድረግ የሕግ መብት ግን የለም፣ ካፍም ፊፋ ጋርም የለም፣ አሁንም ግን አንዳንድ ክለቦች ፈልገው ነበር ሕጉ በፍጹም ተመልሶ አይመጣም ሕገወጥ ነው» ሲሉ አብራርተዋል።


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ማስታወቂያ (CB003/2016)

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የከብቶች ቀለብ (መኖ) አቅርቦት በሀገር አቀፍ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በጨረታው ላይ መሳተፍ የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሁሉ መወዳደር ይችላሉ፡፡

| ተ. ቁ | የግዥው ዓይነት | የጨረታው መለያ ቁጥር | የጨረታ ማስከበሪያ / በብር | የጨረታው መዝጊያ | | የጨረታው መክፈቻ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ቀን | ሰዓት | ቀን | ሰዓት |
| 1 | የከብቶች ቀለብ (መኖ) አቅርቦት | NCB001/ 2016 | 10,000.00 | ለ16ኛው ቀን | 4፡15 | በ16ኛው ቀን | 4፡30 |

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበት ህጋዊና የዘመኑን ግብር ከፍለው የታደሰ ንግድ ፍቃድ፤ በመንግስት ግዥ ላይ ለመሳተፍ የተመዘገቡበት የአቅራቢነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (ቲን) ምስክርወረቀት፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት እና የግብር ክሊራንስ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር100.00 /አንድ መቶ ብር/ ብቻ በመክፈል ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 16 ቀናት ውስጥ ዘወትር በስራ ሰዓት ሸገሌ በሚገኘው በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ግዥ ዲፓርትመንት ቢሮ ድረስ በመምጣት መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ከዚህ በታች በሰንጠረዥ መሠረት በባንክ የተመሰከረለት ሲፒኦ ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ባንክ ጋራንቲ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ስም ሞልተው ከኦሪጅናል የመወዳደሪያ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የሚያቀርቧቸው የፋይናንሺያል አንድ ኦሪጅናልና ሁለት ኮፒ በኢንቨሎፕ ወይም ፖስታ አሽገው የጨረታውን ስምና ቁጥር በመፃፍ ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ተከታታይ እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡15 ድረስ ብቻ በኮርፖሬሽኑ ግዥ ዲፓርትመንት ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ከ4፡15 በኃላ ማለትም የጨረታ ሳጥኑ ከተዘጋ በኃላ የሚመጡ ተጫራቾች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
5. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ቀናት በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡15 ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4 ፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሸገሌ በሚገኘው በኮርፖሬሽኑ ዋናው መ/ቤት ግዥ ዲፓርትመንት ቢሮ ውስጥ ይከፈታል፡፡ ጨረታው የሚከፈትበት ቀን የመንግስት የሥራ ቀን ካልሆነ ወይም ቅዳሜና እሁድ ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ተዘግቶ የሚከፈት ይሆናል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታዉን ዝርዝር ሁኔታዎች ከጨረታ ሰነዱ ላይ የሚያገኙ ሲሆን ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግ በስልክ ቁጥር 011-517-25-21 ደውለው ወይም በአካል መጠየቅ ይችላሉ፡፡
7. ኮርፖሬሽኑ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታው በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡

**የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን**